Addis Ababa University
አዲስ፡አበባ፡ዩኒቨርሲቲ
Seek Wisdom, Elevate your Intellect and Serve Humanity


**በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣**

**የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ አማርኛ ቋንቋ ስነፅሁፍና**

**ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር**


# በሚቄ እና በአንዘቻ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነት እና የውጤት ተዛምዶ (በአስረኛ ክፍል ጉራጌኛ አፈፊት ተማሪዎች ተተኳሪነት)


**በ**

**ሰፊነሽ ባርሳዊ**


**አዲስ አበባ**

**ጥቅምት 2016 ዓ.ም**

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣
የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ አማርኛ ቋንቋ ስነፅሁፍና
ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በሚቂ እና በአንዘቾ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነት እና የውጤት ተዛምዶ (በአስረኛ ክፍል ጉራጌኛ አፈፊት ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በሰፊነሽ ባርሳዊ

የጥናቱ አማካሪ
ዶ/ር ሙላት አሰናቀ

ጥቅምት 2016 ዓ.ም

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣

የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ አማርኛ ቋንቋ ስነፅሁፍና

ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በሚቂ እና በአንዘቻ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነት እና የውጤት ተዛምዶ (በአስረኛ ክፍል ጉራጌኛ አፈፈት ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

ሰፊነሽ ባርሳዊ

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም____________________ ፊርማ________________ ቀን__________

የፈታኝ ስም____________________ ፊርማ________________ ቀን__________

የፈታኝ ስም____________________ ፊርማ________________ ቀን__________

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ እንድሰራ ከጅማሬው እስከ ፍፃሜው ለረዳኝ ፈጣሪዬ ምስጋና ይገባው፡፡ በመቀጠል ይህን ጥናት ከትልመ ጥናት ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ እንደአባት ከጎኔ በመሆን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ገንቢ አስተያየት በመስጠት ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶክተር ሙላት አስናቀ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ እንዲሁም ለዚህ ጥናት የሚያስፈልገኝን ወጪ ድጋፍ ላደረገልኝ እና ላስተማረኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሀሳብም ለጥናቱ አስፈላጊውን ወጪ በመሸፈን ለተባበረኝ ውድ ወንድሜ ልባዊ ምስጋናዬ አቀርባለሁ፡፡

ለጥናታዊ ፅሁፉ አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ የሚቂ እና የአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሰረኛ ክፍል ተማሪዎች፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና የትምህርት ቤቶቹ ርዕሰ-መምህራን ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም መረጃውን በመሰብሰብ ሂደት መጠይቁ በማስሞላት፣ ፈተና በማስፈተን እና በማረም ለተባበሩኝ ለወ/ ሮ ሰርካለም ዘገየ፣ ለወ/ሮ አሚና ዲንሰፋ፣ ለወ/ሮ በላይነሽ አንዷለም እና ለአቶ አሸናፊ ወንድሙ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በተጨማሪም የእስታቲክስ ስሌቱን በማሳየትና በማገዝ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ላደረጉልኝ ለአቶ መሀመድ ደረሰ እና የእኖር ኤነር ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሀላፊ የሆኑ ኤልያስ ሽምሱ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

# ማውጫ


ገጽ

ምስጋና ....... i
ማውጫ ....... ii
አጠቃሎ ....... iv
ምዕራፍ አንድ ....... 1
መግቢያ ....... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ....... 1
1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....... 4
1.3.የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ....... 5
1.4 የጥናቱ ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች ....... 6
1.4.1.የጥናቱ ዋና ዓላማ ....... 6
1.4.2.የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ....... 6
1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ ....... 6
1.6.የጥናቱ ወሰን ....... 7
1.7. የጥናቱ ውሱንነት ....... 7
1.8.የቁልፍ ቃላት ብያኔ ....... 7
ምዕራፍ ሁለት ....... 9
ክለሳ ድርሳናት ....... 9
2.1 የተነሳሽነት ፅንሰ ሀሳብ ....... 9
2.2. የተነሳሽነት አይነቶች ....... 10
2.3. የሁለተኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት ....... 11
2.4. ሁለተኛ ቋንቋን መማር ተነሳሽነት አይነቶች ....... 13
2.4.1 ውህዳዊ ተነሳሽነት ....... 13
2.4.2 ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ....... 14
2.4.3 ውስጣዊ ተነሳሽነት ....... 14
2.4.4 ውጫዊ ተነሳሽነት ....... 14
2.5. የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ... 15
2.5.1. ጥቅማ ጥቅማዊና ውህዳዊ ተነሳሽነት ....... 15
2.5.2.ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ....... 15
2.5.3.ውስጣዊና ውጫዊ ተነሳሽነት ....... 16
2.6.የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ....... 16
ምዕራፍ ሶስት ....... 20
የአጠናን ዘዴ ....... 20
3.1 የጥናቱ ንድፍ ....... 20
3.1.1 የናሙና አመራረጥ ....... 20
3.1.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ....... 21

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች.......................................................................................23
3.2.1 የፅሁፍ መጠይቅ.......................................................................................................23
3.2.2 የችሎታ መለኪያ ፈተና.............................................................................................25
3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ.................................................................................................26
ምእራፍ አራት..................................................................................................................27
የመረጃ ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ .................................................................................27
4.1 የመረጃ ውጤት ትንተና .................................................................................................27
4.1.1 የተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ.........................................................................................27
4.1.2 የ ሁለቱም ትምህርት ቤቶች የፈተና ውጤት.........................................................................28
4.1.3 የተነሳሽነት አይነቶች ውጤት በገላጭ እስታቲስቲክስ .................................................................28
4.1.4 የሁለቱም ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተነሳሽነትና የውጤት ተዛምዶ .............................................29
4.1.5 በሚቄና በአንዘቸ ትምህርት ቤቶች መካከል ያለው አማካይ አማርኛ የመማር ተነሳሽነት ውጤት .........................................................................................................................31
4.2 የውጤት ማብራሪያ ......................................................................................................32
4.2.1 በሚቄና በአንዘቸ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጉራጊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በእያንዳንዱ ተነሳሽነት ያላቸው ተነሳሽነት ምን ያህል ነው?.....................................................................................32
4.2.2 ሚቄና የአንዘቸ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነታቸው ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል?....33
4.2.3 በሚቄና በአንዘቸ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አማርኛን የመማር ተነሳሽነት ልዩነት አለ?...........................................................................................................................33
ምእራፍ አምስት ..............................................................................................................34
ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳብ.........................................................................................34
5.1 ማጠቃለያ..................................................................................................................34
5.2 የመፍትሔ ሀሳብ ........................................................................................................35
ዋቢ ጽሑፎች ...................................................................................................................36
አባሪዎች .........................................................................................................................39

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማው የጉራጊኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸውን ተነሳሽነትና የትህርት ውጤት ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በጉራጌ ዞን በእኖር ኤነር መገር ወረዳ ውስጥ ከሚገኙት ትምህርት ቤቶች በሚቄና በአንዘቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2015 ዓ.ም በመማር ላይ ያሉት 80(ሰማኒያ) የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ተጠኚ ተማሪዎችም በእድል ሰጭ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ የፅሁፍ መጠይቅና ፈተና በመረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጡ ሲሆን ከተጠኚ ተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቅና በፈተና የተሰበሰቡ መረጃዎች በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተተንትኖ ተብራርቷል፡፡ በጥናቱ መረጃ ትንተና መሰረት የተገኘው ውጤት አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የመማር ተነሳሽነት እና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መካከል ዝምድና የታየው ከውህዳዊ ተነሳሽነት ጋር ብቻ (የፒ ዋጋ 0.000) ነው፡፡ ሌላው አማርኛን የመማር ተነሳሽነት በትምህርት ቤትና በትምህርት ቤት መካከል ልዩነት አልታየም፡፡ የጥናቱ ውጤት መነሻ በማድረግ የተማሪዎችን አማርኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ለማሻሻል አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ትምህርቱን ሲያቀርቡ የተማሪዎችን ፍላጎት በሚያነሳሳ መልኩ ቢያቀርቡ እና በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት በፆታ ልዩነት እንዳይፈጠር የወንድና የሴት ተማሪዎች ፍላጎት በመለየት ድጋፍ ቢደረግላቸው የተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ሊሻሻል ይችላል የሚሉትን የመፍትሔ ሀሳቦች ተቀምጧል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

በዚህ ክፍል  የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰንና የቁልፍ ቃላት ብያኔ ተገልፀዋል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ አንደበታዊ፣ ስርዓታዊ እና ድምፃዊ የሰብዓዊ ፍጡር መግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡ ይህ መግባቢያ በሰዎች ማህበራዊ ተራክቦ ወይም ስርዓት ላይ የሚደረገው ግንኙነትና በአጠቃላይ የህብረተሰብን እሴት አካቶ የያዘ ማንነትን በማሳየት በኩል የጎላ ድርሻ ያለው ነው፡፡ስለሆነም ሰዎች ይህንን መግባቢያ በተገቢ ሁኔታ ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡ የተበላሸውን ለማስተካከል ጥሩውን ለማጠናከር ጥቅሙ ብዙ ስለሆነ የቋንቋ አገልግሎ የተሻለ እንዲጠናከርም የቋንቋ ትምህርት በተመለከተ ጥናትና ምርምር ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ የበለጠ ግን በሁለተኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ላይ ጥናት ቢደረግ ውጤታማ መሆኑን አያጠራጥርም፡፡

ሀርመር (1991) እንደገለጹት ተነሳሽነት የሚባለው አንድ ድርጊት እንዲፈፀም የሚያነሳሳ ከውስጥ የሚመነጭ ሀይል እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ተነሳሽነት በሰዎች ያለ የተፈጥሮ ባህሪ ሲሆን አንድ ተግባር ለመፈፀም የሚያግዝ ከውስጥ የሚመነጭ ጉጉት ነው ብሮውን(1987)፡፡ ከነዚህ ምሁራን ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ተነሳሽነት ዓላማን መሰረት በማድረግ አንድ ተግባር ለምን እና እንዴት እንደ ሚፈፀም በባህሪ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥር የሚችል ሀይል እንደሆነ ማወቅ ይቻላል፡፡

ጋርደነር (1985) ተነሳሽነት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ የትምህርት ውጤት ለመግለፅ እንደሚያገለግል አስረድተዋል፡፡ ጋርደነር ከዚህ ሀሳብ ተጨማሪ ያደረጉት ተነሳሽነት ከሁለተኛ ቋንቋ መማር ዘዴ እና ከትምህርት ውጤት ጋር በግልፅ እንደሚገናኝ ገልፀዋል፡፡ በጋርደነር አገላለፅ  የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ጥረት  ሁለተኛ ቋንቋ መማር  ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ የቀና አመለካከቶች ውህደት ነው ይላሉ፡፡ ይህ ሲባል የሰው ልጆች ምኞት እና ዝንባሌ የሚያሳይ አንድን ተግባር መፈፀም እንዲቻል የሚጠናከር መሆኑ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ተስፋዬ ኦላና (2014) እንደገለፁት "ተነሳሽነት የሰዎችን ምኞት ና ጉጉት የሚገልፅ ከውስጣዊ እና ከውጫዊ ፍላጎት በመነሳት በጎ አመለካከትና ጥሩ ውጤትን ሊያስገኝ የሚችል ና አንድ ተግባር እንዲፈፀም የሚያነሳሳ እነደሆነ ያመለክታል፡፡" በማለት ገልፀው በዚህም መሰረት ተነሳሽነት ቋንቋው ለመማር ካለው ፍላጎትና ከሚፈፀመው ድርጊት ለሚገኘው ደስታ የሚከናወነው ስራ

እንደሆነ ገልፀዋል።በተጨማሪም ዘሪቱ (2003) ጋርደነርን(1985) ጠቅሰው ጉጉትና ጥረት ተነሳሽነት የሚከሰትባቸው መንገዶች አንዱ ነው ካሉ በኋላ እነዚህ ለብቻቸው የተነሳሽነትን መኖር አያመለክቱም ብለዋል። ዘሪቱ(2003) አክለውም መነሳሳት ያላቸው ሰዎች ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ሊጥሩ ይችላሉ። ነገር ግን ጥረት የሚያደርጉ ሰዎች በሙሉ ተነሳሽነት ሊኖራቸው አይችልም በማለት አስረድተዋል። ዘሪቱ ተነሳሽነት አለ የሚባለው ዓላማን ከግብ የማድረስ ፍላጎት እንዲሁም ለዓላማው ያለውን ጥሩ አመለካከት ከጥረቱ ጋር መገናኘት ሲችል ነው በማለት ገልፀዋል።

ብሮውን (2000) ሁለት አይነት የሁለተኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት እንዳሉ ይገልፃሉ። እነሱም ውህዳዊ ተነሳሽነት እና ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ናቸው በማለት በሁለት ይከፍሉታል። ውህዳዊ ተነሳሽነት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋው ከሚናገሩ ማህበረሰቦች ለመቀላቀልና ለመቀራረብ ሲሉ እና የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ኑሮ፣ ወግ እና ልማድ ለማወቅ ሲሉ ቋንቋውን የሚማሩበት የተነሳሽነት አይነት እንደሆነ ኢሊስ (1995) ገልፀዋል።

ሌላኛው የተነሳሽነት አይነት ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት የሚባለው ነው። ይህ የተነሳሽነት አይነት የቋንቋ ተማሪው የተለያዩ ጥቅሞችን ለማግኘት ሲል ቋንቋው የሚማርበት ነው ኢሊሰ (1995)።ኖሪስ (2001) የዚህ የተነሳሽነት አይነት ዋና ዋና ኣላማዎች የሚባሉተ ብዙ ግዜ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተሻለ ክፍያ ለማግኘት፣የተለያየ እውቀት ለማግኘት እና ዩኒቨርሲቲ ለመግባት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ሲሉ ቋንቋውን እንደሚማሩ ገልጸዋል።

ውስጣዊ እና ውጫዊ የተነሳሽነት አይነቶች በሙህራን ተደጋግሞ የሚነሱ የተነሳሽነት አይነቶች ሲሆኑ ውስጣዊ ተነሳሽነት የሚባለው ተማሪዎች የሚያስተምሯቸው መምህራን የሚያስተምሩበት ዘዴው ቢያስደስታቸውም ባያስደስታቸውም ቋንቋው ለመማር የሚነሳሱበት የተነሳሽነት አይነት እንደሆነ ብሮውን (2000) ገልፀዋል።

ውጫዊ ተነሳሽነት ሌላኛው የተነሳሽነት አይነት ሲሆን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከሌላ አካል ውዳሴ ለማግኘት፣ ለመወደድ፣ለጥፋት ላለመዳረግ እና ላለመቀጣትና የመሳሰሉ ዓላማዎችን ለማሳካት ሁለተኛ ቋንቋው የሚማሩበት ነው በሮውን (2000)።

የውጫዊ ተነሳሽነት ዓላማዎች ብር፣ ማዕረግ እና ማርክ እንደዚሁም  አሉታዊ ያልሆኑ ምላሾች ማግኘት ናቸው። ስለዚህ የተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ  የመማር ተነሳሽነት ማጥናቱ በተለያዩ ተመራማሪዎች የተጠቀሱትንና ስኬትን የሚያጠፉ ችግሮች በማቃለል የተማሪዎችን ስኬታማነት ወደፊት ያራምዳል።

በተስፋዬ (2014) የተጠቀሱት ጋርድር ና ላምቤርት (1997) የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለውን  ዝምድና ለመመርመር ጥናቶች ያካሄዱ እና የምርምር መሪ የሆኑት ተመራማሪዎች በአሜሪካዊያን ዓውድ ውስጥ ከእንግሊዝኛ እና ፈረንሳይኛ ቋንቋ  ተናጋሪ ማህበረሰብ በመጡት ና ፈረንሳይኛ ቋንቋ እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ናሙናዎችን ወስደው የሁለተኛ ቋንቋ ተለዋዋጮችን ና  የትምህርት ውጤት ተዛምዶ በሚመለከት ምርምር አድርገዋል። በጥናቱም ውጤት የቋንቋ ተሰጥኦ የተነሳሽነት መጠን ና የፈረንሳይኛ ቋንቋ ለመማር ያለ ምኞትን በተመለከተ ከተጥኚዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ተለዋዋጮች ከትምህርት ውጤት ጋር ያላቸው ተዛምዶ ዝቅተኛ እንደሆነ ገልፀዋል።

ተነሳሽነትና የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ተዛምዶን በተመለከተ አንድ ተማሪ በትምህርቱ አጥጋቢ ውጤት ሚያስመዘግበው ሁለተኛ  ቋንቋ ትምህርት ለመማር ፍላጎት ካለውና ፍላጎቱም ለማሳካት ሲጥር ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ ይህ  ተማሪ  ቋንቋው ለመጠቀም ጥሩ ችሎታ እንዳለው  ይታሰባል።

በአጠቃላይ ዊሊያም እና ቡርደን (1997) እንደገለፁት ተነሳሽነት አንድ ድርጊት ለማድረግ ውሳኔዎችን ለመስጠት የሚመራ የአእምሮ ጥረት እንዲያነሳሳ የሚያደርግ ቀድሞ የታቀደው ስኬት እንዲሳካ የሚያደርግ እንደሆነ ገልፀዋል። እንዲሁም በመስኩ ምሁራን በተደጋጋሚ የሚነሱ የሁለተኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት አይነቶች አራት ናቸው። እነሱም  የመጀመሪያው ውህዳዊ ተነሳሽነት ሲሆን ሁለተኛ ቋንቋ የሚማር ተማሪ ቋንቋው የሚማረው ከሁለተኛ ቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ወግ እና ልማድ ለመተሳሰር ቋንቋው ከተማር ይህ ተማሪ ያለው የተነሳሽነት አይነት ውህዳዊ ተነሳሽነት ይሆናል። ሌላው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ቋንቋውን የሚማረው በተማረው ቋንቋ ጥቅማ ጥቅምን ተስፋ በማድረግ ከተማረ የተማሪው ተነሳሽነት ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ይባላል ጋርድነር እና ላምቤርት(1972)። እንዲሁም አንድ ሰው የሚሰራውን ስራማወቅና መረዳት

ከፈለገ እና ደስታ እንዲያገኝ ቋንቋውን ከተማረ ተነሳሽነቱ ውስጣዊ ተነሳሽነት ነው፡፡ በሌላ አካል ለመመስገን እና ለመወደስ ሲል ሁለተኛ ቋንቋ የሚማረው ተማሪ ውጫዊ ተነሳሽነት ያለው ተማሪ ነው ናካሙራ(1989)፡፡

## 1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች አማርኛን በመማር ተነሳሽነት ዙሪያ ጥናት ማድረግ በተማሪዎች ተነሳሽነት ላይ የሚፈጠውን ችግር በማስወገድ ውጤታማነት የሚሆንበትን መንገድ በማመቻቸት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ተነሳሽነት በሁለተኛ ቋንቋ በመማር ስርዓት ተማሪው በትምህርቱ ጥሩ ውጤት እንዲኖረው ማድረግ ይችላል፡፡ ሊትልዉድ(1981) እንደገለፁት ቋንቋ መማር በቅድሚያ የማነሳሳት እና ተማሪዎቹ ከትምህርቱ ያገኙትን እውቀት ዘላቂ እንዲሆን ለማገዝ እና የሁለተኛ ቋንቋን ለመልመድ እንዲጠናከር ተነሳሽነት ከፍተኛ ሚና እንዳለው ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ተነሳሽነት እንጂ ሌሎች ነገሮች ተግባራዊነት የላቸውም በማለት ተናግረዋል፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ተነሳሽነት የሚኖራቸው ተማሪዎችን በቋንቋ ትምህርት ስርኣት ውስጥ ተሳትፎ እንዳላቸው እና በድርጊቱም እንደሚጠቀሙ የተሻለ እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

ጋርደንር(1985) ተነሳሽነት በአመለካከት እና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል የሚታየውን ዝምድና ያመቻቻል ይላሉ፡፡ ይህንን ሀሳብማረጋገጥ እንዲችሉ በሁለት ቦታ ባደረጉት ጥናት መረጃ ሰብስበው በተነሳሽነት ላይ ተፅዓኖ የሚፈጥሩ አላባዊያን በምርምሩ ባልተካተቱ ሁኔታየአመለካከት ልኬታዎችና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት መሀል ያለው የዝምድና ልክ እንደሚቀንስ ተናግረዋል፡፡

በሃገራችንም የአማርኛ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ በዘሪቱ (2003) በተጠናው ምርምር ተማሪዎቹ ከፍተኛ ተነሳሽነ(147.93) ቢኖራቸውም የፈተና ውጤታቸው (41.99) ስለሆነ ዝቅተኛ መሆኑን ተገልፀዋል፡፡ ይህም ማለት በተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነት እና በትምህርት ውጤታቸው መካከል ተዛምዶ አልታየም፡፡ በተጨማሪም ተነሳሽነት በተመለከተ ክፍሌ (2002) ባካሄደው ምርምር በተማሪዎች ውስጣዊ ተነሳሽነት ና በትምህርት ውጤት መካከል ጉልህ ተዛምዶ(የፒ ዋጋ 0.002) መኖሩን ገልፀዋል፡፡ ውጫዊ ተነሳሽነት በጥናቱ የትምህርት ውጤት ተንባይ ሆኖ እንዳልተገኘ አመልክቷል፡፡እንዲሁም ተስፋዬ ኦላና(2014) ባጠናው ጥናት በተማሪዎች ጥቅማ ጥቅማ ተነሳሽነት( የፒ ዋጋ 0.08)

ከላይ ከተቃኙት ጥናቶች ሁለቱ በተነሳሽነትና በትምህርት ውጤት ዙሪያ ያተኮሩ በመሆናቸው ይመሳሰላሉ፡፡ ይህ ጥናት ደግሞ ተነሳሽነት ና የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ግንኙነት ላይ ስለሚያተኩር ከክፍሌና ከዘሪቱ ጥናት ጋር ይቀራረባል፡፡

በየጊዜው በተለያዩ ተመራማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት በተመለከተ ጥናቶችን ተካሂደዋል፡፡ እነዚህ ተመራማሪዎች ሁሉ ግን አንድ የሚያደርጋቸው የጋራ ግኝት አለ ብሎ ማለት አይቻልም፡፡ ከዚህም በመነሳት የሁለተኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ስኬታማ እንዲሆን አሁንም ስለተነሳሽነት እና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ ማጥናት ተገቢ መሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ለዚህ ጥናት መካሄድ የመጀመሪያው አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ጥናት እንዳካሄድ ያነሳሳኝ ሁለተኛው ምክንያት በዚህ አካባቢ በመምህርነት ሙያ ሳገለግል በቆየሁበት ጊዜ በትምህርት ቤቶቹ በጉራጊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ አብዛኞቹ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ዝቅተኛ መሆኑ ተገነዘብኩ፡፡ በዚህም የተነሳ የተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታቸው በጉራጊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን የሁለተኛ ቋንቋን ትምህርት ውጤታቸው ቋንቋውን ለመማር ከሚኖራቸው መነሳሳት ጋር ያለው ዝምድና ምን ያህል ነው? የሚለው ጥያቄ በአእምሮዬ ውስጥ ስለተፈጠረ ሲሆን ሶስተኛው አነሳሽ ምክንያት ደግሞ ይህንን ጥናት በሚካሄድበት ቦታ በዚህ ርዕስ ላይ ጥናት ያልተካሄደ መሆኑ ይህ ጥናት ለማካሄድ ያነሳሱኝ ምክንያቶች ናቸው፡፡

### 1.3.የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

በዚህ ጥናት ምላሽ እንዲፈለግላቸው የታሰቡ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በሚቂና በአንዘቻ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በጉራጊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ አማርኛ ቋንቋ እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በእያንዳንዱ ተነሳሽነት አይነት ያላቸው ተነሳሽነት (motivation) ምን ያህል ነው?

የሚቂና የአንዘቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን መማር ተነሳሽታቸው ከትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ (correlation) ምን ይመስላል?

3.በሚቂ ና በአንዘቻ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መካከል አማርኛን የመማር ተነሳሽነት ልዩነት አለ?

## 1.4 የጥናቱ ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች

### 1.4.1.የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማው በሚቴ ና በአንዘቸ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የጉራጊኛ ቋንቋ አፌ-ፌት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነት ና የትምህርት ውጤት ተዛምዶን መፈተሽ ነው፡፡

### 1.4.2.የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

የሚቴና የአንዘቸ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመማር ያላቸውን ተነሳሽነት መለየት፡፡

የተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነት ከቋንቋው ትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና ምን ያህል እንደሆነ ማረጋገጥ፡፡

የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነት በትምህርት ቤትና በትምህርት ቤት መካከል ያለውን  ልዩነት ለመለየት፡፡

### 1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉትን ፋይዳዎች እንደሚኖሩት ይታመናል፡፡

ተማሪዎች በጥናቱ ውጤት መሰረት በአማርኛ ትምህርት ውጤታማ የሚያደርጋቸውን የተነሳሽነት አይነት ለመከተል ጥረት እንዲያደርጉ ሊያነሳሳ ይችላል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማር ላይ ተነሳሽነት የሌላቸው ተማሪዎች አስፈላጊ  እገዛ በመስጠት ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ሊያበረታታ ይችላል፡፡

በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነትና በቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል የሚኖረውን ተዛምዶ ለማወቅና ከዚህም ተጠቃሚ ለመሆን ለሚፈልጉ ተማሪዎች፣ መምህራን ና ተመራማሪዎች ጠቃሚ መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡

በጥናቱ ውጤት መሰረት አማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንደ ሁለተኛ ቋንቋነት የሚያስተምሩ መምህራን በወንድና በሴት መካከል የተነሳሽነት  ልዩነት መኖሩና አለመኖሩን ተረድተው የመማር ማስተማሩን ዘዴ   ለመከተል የሚያግዝ መረጃ ሊሆን ይችላል፡፡

ወደፊት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ና በተነሳሽነት ዙሪያ ለሚሰሩ ጥናቶች መሰርት በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተካሄደው በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ማለትም በእኖር ኤነር መገር ወረዳ በሚቁና በአንዘቾ ሁለተኛ ደርጃ ትምህርት ቤቶች በሚማሩ የክፍል ደረጃቸው አስረኛ ክፍል በሆኑ ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን ጥናቱ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ብቻ የተገደበው አጥኚዋ የምትሰራበት አካባቢ ከመሆኑ በተጨማሪ ካለው የአቅም ና የጊዜ ማጣት የተነሳ ነው፡፡

ይህ ጥናት በሂደት ያካተታቸው ተለዋዋጮች አማርኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነትንና የ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ናቸው፡፡ በሚቁና በአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሉ የሁለቱም ፆታ አስረኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማር ያላቸውን ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለው ዝምድና መርምሯል፡፡ ስለዚህ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነት እና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ ላይ ብቻ ተካሂዷል፡፡ ጥናቱ የተከተለው ተዛምዷዊ ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም ያለው(1996) እንደገለፁት ተዛምዷዊ ጥናት በሁለት ከሁለት በላይ በሆኑ ተለዋዋጮች መካከል ያለውን የግንኙነት አቅጣጫ ና ልክ መወሰን ያስችላል በማለት ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ በዚህም ጥናት በተለዋዋጮች መካከል ያለውን የዝምድና መጠን ተቀመጧል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ውሱንነት

በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የመሰናዶ ተማሪዎች በትናቱ ተሳታፊ ለማድረግ ተሞክሮ ነበር ፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ ተማሪዎች መጠይቁ ለመሙላት እና መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ ፍቃደኛ ስላልሆኑ በትናቱ ውስጥ ሳይካተቱ ቀርተዋል፡፡ ይህም በጥናቱ ውስጥ እንደውሱንነት ይታያል፡፡ ሌለው የጥናቱ ውሱንነት ከሚቁ እና ከአንዘቾ ትምህርት ቤቶች በናሙናነት ከተመረጡ 83 ተማሪዎች ውስጥ ሶስት ተማሪዎች መጠይቁን ሲሞሉ በመመሪያው መሰረት ባለመሙላታቸው እና መጠይቁን በግዴለሽነት በመሙላታቸው የተሳሳተ ተብሎ ስለተያዙ በመጠይቁ ውስጥ አልተካተቱም፡፡

## 1.8.የቁልፍ ቃላት ብያኔ

**ተዛምዶ፦** የጉራጊኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ሲማሩ ቋንቋውን ለመማር ባለቸው ተነሳሽነት እና በውጤታቸው መካከል የሚኖረውን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ግንኙነት ይመለከታል፡፡

**ተነሳሽነት፦** የጉራጊኛ ቋንቋ አፊ-ፊት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ሲማሩ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው አመለካከት ፣ፍላጎት ፣ ስሜት ፣ ጉጉት ፣ ምኞት ና ጥረት ይመለከታል፡፡

**የትምህርት ውጤት፦** አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የጉራጊኛ ቋንቋ አፊ-ፊት ተማሪዎች የሚኖራቸውን የተነሳሽነት መጠን ና አይነት ተከትሎ በቋንቋ ትምህርት ፈተና ያስመዘገቡትን ውጤት ያመለከታል፡፡

**ውስጣዊ ተነሳሽነት፦** የጉራጊኛ ቋንቋ አፊ-ፊተ የሆኑ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት ሲማሩ ተማሪዎች ቋንቋውን እንዲረዱ ና በቋንቋው የሚያደርግ ተፈጥሯዊ ግፊት ስሜት ነው፡፡

**ውጫዊ ተነሳሽነት፦** አማርኛ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ስለቋንቋው እንዲያውቁ ፣ እንዲረዱ ና ለመግባባት እንዲችሉ በሚያገኙት ጥቅሞች አማካኝነት ቋንቋውን ለመማር የሚያሳዩትን የመገፋፋት ስሜት ውጫዊ ተነሳሽነት ይባላል፡፡

**ውህዳዊ ተነሳሽነት፦** በተነሳሽነት መለኪያ መሰረት አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ከአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህል ጋር ለመተሳሰር ያላቸውን ፍላጎትና ቀና አመለካከትን ይገልፃል፡፡

**ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት፦**በተነሳሽነት መለኪያ መሰረት ጉራጊኛ አፊ-ፊት የሆኑ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ሲማሩ ለተግባራቶች ምክንያት የሚያሳዩት ትግል ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት
# ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተነሳሽነትና የተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትና የትምህርት ውጤት (education result) ተዛምዶ (correlation) በተመለከተ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች እንደሚከተለው ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ እነሱም ፦ የተነሳሽነት ምንነት፣ የተነሳሽነት አይነቶች፣ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት፣ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት አይነቶች፣ ተነሳሽነት ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ፣ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል ያለው የተነሳሽነት ልዩነት እና የቀደምት ጥናቶች ቅኝት የሚመለከቱ ናቸው፡፡

## 2.1 የተነሳሽነት ፅንሰ ሀሳብ

ተነሳሽነት የሚለው ፅንሰ ሀሳብ በርካታ ምሁራን የተለያዩ ገለፃዎች ሲያስቀምጡ ይስተዋላል፡፡ ከነዚህ የሙህራን ገለፃዎች የሚከተሉት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ዊሊያም እና ቡርደን (1997) እንደገለፁት በንቃተ-ህሊና አንድን ተግባር ለማከናወን የሚደረግ እና ጥረቶችን የሚያጠናክር ስነ- ልቦናዊ ቅስቀሳ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

ብሮውን (2000) የተነሳሽነት ምንነት ከባህሪያዊያን፣ ከአእምሮታዊን እና ከግንባታዊያን እይታዎች አንፃር ብያኔዎች አስቀምጠዋል፡፡

ተነሳሽነት (motivation) ከባህሪያዊያን እይታ አንፃር አንድ ተግባር ለማከናወን ማጠናከሪያ በመስጠት ምላሽ እንዲሰጥ ከማድረግ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

ከአእምሮታዊያን እይታ አንፃር ተነሳሽነት የሚመነጨው ከባለቤቱ ከራሱ ነው፡፡ የአእምሮታዊያን እይታ ከግንባታዊያን እይታ አንፃር ሲታይ ተነሳሽነት የሚመሰረተው በሰዎች ህግና ደንብና ምርጫ ላይ መሆኑን ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ብሮውን (2000) በእነዚህ እይታዎች መካከል ያለውን ልዩነት በሚከተለው ሰንጠረዥ አስፍረውታል፡፡

**ሠንጠረዥ "ሀ" ባህሪያዊያን፣ አእምሮታዊና ግንባታዊያን ከተነሳሽነት አንፃር ያላቸው አተያይ**

| ባህሪያዊያን | አእምሮታዊያን | ግንባታዊያን |
|---|---|---|
| ማበረታቻ በመስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ | በራስ ምርጫ የተመሰረተ ነው፡፡ | በህብረተሰቡ ስርዓት ላይ ይገነባል፡፡ |
| በውጫዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ይመሰረታል፡፡ | ውስጣዊ ስለሆነ በግለሰቡ ይመራል፡፡ | ውስጣዊ ሆኖ በተራክቧዊ ሁነቶች ላይ ይመሰረታል፡፡ |

በሰንጠረዥ ሀ ላይ የተገለፀው ተነሳሽነት ከባህሪያዊያን፣ ከአእምሮታዊያን እና ከግንባታዊያን እይታዎች አንፃር ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት ተነሳሽነት የሚፈጠርበትን መንገድ እንደ ቋንቋ ትምህርት ስርዓት በባህሪያዊያን እይታ ሲታይ ለቋንቋ ተማሪው የተለያ ማበረታቻዎች እየተሰጠው በመማሩ ተማሪው ቋንቋውን የመማር ተነሳሽነቱ ይጨምራል፡፡

ሌላው አእምሮታዊያን እንደሚሉት በቋንቋ ትምህርት ላይ ምንም አይነት ውጫዊ ተፅዕኖ ሳይኖር በግለሰቡ ውጣዊ ፍላጎት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል ይላሉ፡፡ እንዲሁም በግንባታዊያን እይታ ተማሪው በቋንቋው መማር ላይ ባለው ተነሳሽነት እንዲሁም በሚፈፅመው ድርጊት በተማሪው ተነሳሽነት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

## 2.2. የተነሳሽነት አይነቶች

በርካታ ምሁራን ተነሳሽነትን በተለያዩ መንገዶች ከፋፍለው ያስቀምጧቸዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ብሮውን (2000) ተነሳሽነት ውስጣዊ እና ውጫዊ ተነሳሽነት በማለት በሁለት ክፍለው ያስቀምጧቸዋል፡፡

የመጀመሪያው ውስጣዊ ተነሳሽነት የሚባለው ሲሆን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ቋንቋን የሚማረው በተማረው ቋንቋ ጥቅማ ጥቅሞች ተስፋ በማድረግ ወይም ከግለሰቡ ውጪ ሆነ አካል ተገፋፍቶ ሳይሆን ቋንቋው ሲማር ከሚያገኘው ደስታ ተነስቶ በራሱ ልዩ ለዩ ተግባራት ለመተግበር የሚያጥርበት ነው፡፡ በመሆኑም ውስጣዊ ተነሳሽነት ያለው ተማሪ ቋንቋውን የሚማረው ውስጣዊ የመማር ፍላጎቱን መነሻ በማድረግ ነው፡፡

ሁለተኛው ውጫዊ ተነሳሽነት የሚባለው ደግሞ የሁለተኛ ቋንቋ በዚህ ተነሳሽነት አይነት ሁለተኛ ቋንቋ የሚማረው በሌላ አካል ከሚያገኘው ማበረታቻ እና ድጋፍ መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ይህ

አይነቱ ተማሪ በሌላ አካል ማበረታቻ የሚመሰረት ስለሆነ በሌላ አካል ካልተገፋፋ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ላይ ደካማ ይሆናል፡፡

ከላይ ከተገለፁት የምሁራን አስተያየት መሰረት አንድ ተግባር ለምን እንደሚፈፀም የሚያመለክት ውስጣዊ ግፊት ተነሳሽነት ይባላል፡፡

## 2.3. የሁለተኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት

ዓላማ መነሻ አድርጎ አንድ ነገር ለምን እንደሚፈፀም ና በምን አይነት ሁኔታ እንደሚፈፀም የሚያመለክት በባህሪ ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆነ ከስውጥ የሚመነጭ ሀይል ተነሳሽነት ይባላል፡፡

ኢሊስ(1995) እና ጋርድነር(1985) ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የትምህርት ውጤታቸው መወሰን የሚቻለው ተማሪዎቹ ታላሚውን ቋንቋ ለመማር በሚኖራቸው የተነሳሽነት ልክ እና አይነት ነው በማለት ተመራማሪዎቹ ገልጸዋል፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ ከሚማሩበት ዋና ዋና ዓላማዎች ውስጥ ከታላሚ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቅርርብ ለመፍጠር ፣ በተማሩት ቋንቋ ጥቅማ ጥቅሞችን እንዲያገኙ በሌላ አካል ለመወደስ ወይም ለመመስገን እና ቋንቋውን በመማራቸው ለመደሰት እና እርካታ ለማግኘት እና ወዘተ. እንደሆኑ ጋርድንር(1985) ገልፀዋል፡፡

ተስፋዬ ኦላና(2014) ኖኤል (2001)፣ ብሮውን (1994) እና ስተርን (1994) በመጥቀስ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋውን የሚማሩበት ሌላው ዓላማ ለመመስገን፣ ለመሸለም፣ እውቅና ለማግኘት ና ወዘተ. ዓላማዎች ለማሳካት ሲሉ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ እንደሚማሩ ያበራራሉ፡፡

ጋርድንር (2001) የሁለተኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት ጥቅማ ጥቅማዊ እና ውህዳዊ ብለው በሁለት ይከፍሉታ፡፡ ከእነዚህም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከቋንቋው ተናጋሪዎች ጋር ማህበራዊ ግንኙነት ለመፍጠር የሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩበት የተነሳሽነት አይነት ውህዳዊ ተነሳሽነት እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ለሁለተኛ ቋንቋቸው እሴት በጎ አመለካከት ስለአላቸው ቋንቋውን ለመማር ከፍተኛ መነሳሳት እንደሚኖራቸው ይታመናል፡፡

ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች በተማሩት ቋንቋ አንዳች ጥቅምን ለማግኘት ሲሉ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩበት እንደሆነ ተመራማሪዎቹ ይናገራሉ፡፡ ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ያላቸውተማሪዎች ቋንቋውን ከሚማሩበት ዓላማዎች ውስጥ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋም ለመግባት የሚያስፈለጉ ነገራቶችን ለማሟላት፣ ዓለም አቀፋዊ መረጃ እና እውቀት የተሻለ ደሞዝተኛ ለመሆን እና ለመሳሰሉት ዓላማዎች ሲሉ ቋንቋውን እንደሚማሩ ጋርደነር(2001)

ያስረዳሉ። ነገር ግን ከሁለቱም የተነሳሽነት አይነቶች የትኛው የተነሳሽነት አይነት ያለው ተማሪ ታላሚው ቋንቋውን በጥሩ ሁኔታ እንደሚማር የተለያዩ ተመራማሪዎች የተለያዩ ሀሳቦችን ሰንዝረውበታል። ከእነዚህም ተመራማሪዎች ውስጥ ጋርደነርና ላምቤርት (1972) እንደገለፁት ከሁለቱም የተነሳሽነት አይነቶች ትቅማ ጥቅማዊ ብዙ ጊዜ ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ካላቸው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋውን የተሻለ የሚማሩት ውህዳዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች እንደሆኑ እንደሚያምኑ አሊስ(1995) ይገልፃሉ። ውህዳዊ ተነሳሽነት ያላቸው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋውን በተሻለ ሁኔታ ይማራሉ ብለው ያምናሉ።

ለረጅም ጊዜ ሁለተኛ ቋንቋ መማር ዓላማ ያላቸው ተማሪዎች ውህዳዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች እንደሆኑ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ። ምክንያቱም ከቋንቋው ተናጋሪዎች ጋር ቅርርብ ፈጥረው እንዲኖሩ ስለሚፈልጉ ቋንቋውን ለመማር ከፍተኛ የሆነ ተነሳሽነት ይኖራቸዋል።

ተስፋዬ ኦላና(2014) እንደገለፁት የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በፍላጎት በመማርና ለረጅም ጊዜ በመጠቀም በኩል ውህዳዊ ተነሳሽነት ሚናው ከፍተኛ ቢሆንም አብዛኛው ተማሪዎች ግን ከውህዳዊ ተነሳሽነት ይበልጥ ለጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ዓላማንቅድሚያ በመስጠት ቋንቋ በመማር ውጤታማነቱን የሚያመዝን ይመስላል ብለዋል። በተጨማሪም በኖሪስ(2001) የተጠቀሱ ሉክማን(1972) የህንድ ተሞክሮዋቸውን መሰረት በማድረግ ውህዳዊ ተነሳሽነት ካላቸው ተማሪዎች ይልቅ ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ያላቸው ከምዕራባዊያንውጪ ያሉ ሴት ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ትምህርት የተሻለ ውጤት እንደስመዘግቡ ገልፀዋል። እንደመረጃ ቀረቡትም አለምአቀፍ መግባቢያ ይዘት ያላቸው እንግሊዘኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ቋንቋውን መሰረት አድርገው የሚማሩበት ኣላማ ከውህዳዊ አላማ ይልቅ ጥቅማ ጥቅማዊ ዓላማ እንደሚመርጡ ገልጸዋል።

ጋርድነር (1985) እንደሚገልፁት ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትን መመርመር ውህዳዊም ሆነ ጥቅማ ጥቅማዊ የተነሳሽነት አይነቶች ከሁለተኛ ቋንቋ መማር ጋር ግንኙነት ሊኖራቸውም ላይኖራችውም የሚችሉ ሶስት አላባዊያን ያሉ ሲሆን እነዚህ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት አላባዊያን የሚባሉት ጥረት፣ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ የመማር አላማን የማሳካት ምኞት ና ሁለተኛ ቋንቋውን ለመማር የሚኖር ጥሩ አመለካከት ናቸው በማለት ገልፀዋል።

ተደጋግሞ የሚነሱ ሌሎች የተነሳሽነት አይነቶች ውስጣዊ ና ውጫዊ የተነሳሽነት አይነቶች ሲሆኑ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ከውስጣቸው በሚፈጠር ግፊት ወይም ሀይል ቋንቋውን

ተምረው የተለያዩ ድርጊቶችን በመፈፀም ደስታ የሚያገኙበት የተነሳሽነት አይነት ውስጣዊ ተነሳሽነት እንደሆነ ኖኢልስ(2001)፣ብሮውን (2000) ገልጸዋል፡፡ የዚህ አይነት ተነሳሽነተ ያላቸው ተማሪዎች የመምህሩ የማስተማር ስልት ቢመችምም ባይመችም፣ ትምህርቱ ፈተና ኖረውም አልኖኖረውም ቋንቋን ለመማር ይነሳሳሉ፡፡ በቋንቋ ትምህርት እና በድርጊቱ አፈፃጸምም ይረካሉ፡፡ እንዲሁም ውጫዊ ግፊት ና ቅስቀሳ ሳይደረግባቸው ከውጣቸው በሚፈጠር ስሜት ተመስርተው ስራዎችን የመስራት ጉጉትት አላቸው በማለት ኖኤልስ(2003) ገልፀዋል፡፡ ሌላኛው የተነሳሽነት አይነት ውጫዊ ተነሳሽነት ሲሆን ኢሊስ (2005) ውጫዊ ተነሳሽነት የሚፈጠረው በጓደኞቹ ወይም በሌላ አካል ለመወደስ ፣ ለመታገዝ፣ ምስጋና ለማግኘት፣ ፈተና ለማለፍ፣ ላለማጥፋት እና ለቅጣት ላለመዳረግ ወዘተ. የአጭር ጊዜ ስኬቶችን ሊያስገኝ የሚችል ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ ኖኤልስ (2003)ውጫዊ ተነሳሽነት ውስጣዊ ተነሳሽነት እንዲቀንስ ተፅእኖ የሚያደግርበት አጋጣሚ አለ ብለዋል፡፡ ፒንትሪቼ (2002) ደግሞ እንደተመራማሪዎች አተያይ ውጫዊ የሆኑ ሽልማቶች ለተማሪው የሚሰጠው ከሆነ በውስጣዊ ተነሳሽነት ለሚፈፀም ተግባር እንዲቀንስ ያደርገዋለ በማለትተናግረዋል፡፡

ኢሊስ (1995) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋው የመማር ተነሳሽነታቸውአነስተኛ ከሆነ ውጤታችም ዝቅተኛ ይሆናል በማለት አስረድተዋል፡፡ እንዲሁም ጋርድነር (2003) የቋንቋ መማር ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤት ጋር እንደሚገናኝ አመላክተዋል፡፡

## 2.4. ሁለተኛ ቋንቋን መማር ተነሳሽነት አይነቶች

ጋርድነርና ላምቤርት(1959) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋውን ሚማሩበትን ተነሳሽነት አይነት በተመለከተ ምርምር ያደረጉ ሲሆኑ እነዚህ ተመራማሪዎች የተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት አይነቶች ውህዳዊ ተነሳሽነት እና ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት በማለት የከፋፈሉት ሲሆኑ በዊሊምስና በቡርደን(1997) ዋቢነት የተጠቀሱ ናካሙራ (1989) ውስጣዊና ውጫዊ የተነሳሽነት አይነቶች አስተዋውቀዋል፡፡ እነዚህም እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 2.4.1 ውህዳዊ ተነሳሽነት

የመጀመሪያው የሁለተኛ ቋንቋ ተነሳሽነት አይነት ውህዳዊ ተነሳሽነት ሲሆን ይህ የተነሳሽነት አይነት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከቋንቋው ተናጋሪዎች ጋር ለመቀላቀል እና ለመቀራረብ እንዲሁም ማህበራዊ ውህደት ለመፍጠር ፈልገው ቋንቋውን ሚማሩበት እና የሚያጠኑበት የተነሳሽነት አይነት ነው፡፡ በተጨማሪ ጋርድነር(1987) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋውን

በመማር የሚሳተፉት የሚፈልጉትን ነገር ካገኙ በኂላ እንደማይቋጥ እና ቋንቋውን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ የሚማሩ መሆናቸውን ያብራራሉ፡፡

### 2.4.2 ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት

ሁለተኛው ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ነው፡፡ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ አንዳች ጥቅማ ጥቅም ማግኘት ሲፈልጉ ቋንቋውን ለመማር የሚነሳሱበት የተነሳሽነት አይነት ነው ኢሊስ(1997)፣ ጋርድነር(1985)፡፡የዚህ አይነት ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ዓላማቸው የተለያየ ይሁን እንጂ አብዛኞቹ ዩኒቨርሲቲ በተሳካ ሁኔታ እንዲገቡ አስፈላጊውን መስፈርት ማሟላት መፈለግ፣ የከፍተኛ ደሞዝ ባለቤት ለመሆን  እና አለምአቀፋዊ መረጃዎች ለማግኘት ሲሉ ቋንቋውን በተሳካ ሁኔታ ይማሩታል በማለት ኖሪስ(2001) ተናግረዋል፡፡

### 2.4.3 ውስጣዊ ተነሳሽነት

ሶስተኛው ውስጣዊ ተነሳሽነት ተማሪዎች ቋንቋውን የሚማሩት በውስጣዊ ግፊት የመማር ተግባራትን  በማከናወን ደስታ እና እርካታ የሚገኝበት የተነሳሽነት አይነት ነው በማለት ኢሊስ(1994) ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎቹ የመምህሩ የማስተማር ስነ-ዘዴ ተመቸውም አልተመቸውም ፣ ትምህርቱ ፈተና ኖረውም አልኖረው ቋንቋውን ከመማር ወደኂላ የማያፈገፍጉበት ነው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ቋንቋውን በመማርና ተግባራቱ በማከናወን እርካታ ያገኛሉ ኖኤል(2003)፡፡

### 2.4.4 ውጫዊ ተነሳሽነት

አራተኛው የተነሳሽነት አይነት ውጫዊ ተነሳሽነት ሲሆን ሰዎች የሚያከናውኑትን ተግባር ከተግባሩ ውጪ ከሆኑ አካል ጋር አዎንታዊ መልስ እንዲያገኙ፣ በትምህርት ጥሩ ውጤት ለማምጣት ወይም ለማስመዝገብ እንዲሁም ለጥፋት ላለመዳረግ ጥረት የሚደረግበትነ ወዘተ. የአጭር ጊዜ ስኬቶችን የሚያሳካ የተነሳሽነት አይነት ነው ኢሊኦት (2005), ብሮውን (1994)፡፡

ዘሪቱ (2003) ጋርድነር(1985) በመጥቀስ እንደአስረዱት በአራቱም ተነሳሽነቶች  አንድ ተማሪ ተነሳሽነት እንዳለው የሚታወቀው መጀመሪያ ተማሪው ዓላማን መሰረት አድርጎ ሲቀሳቀስ  ሲሆን ሁለተኛ ተማሪ ዓላማውን ለማሳካት ጥረት ሲያደርግ ነው፡፡ እነደዚህ ያለው ተማሪ ስለሚያከናውናቸው ስራዎች ሲጠየቅ ለዓላማው ያለው ጉጉት፣ ፍላጎት እና ቋንቋውን ለመማር የሚያስችሉት ተግባራት መልካም አመለካከት ያንፀባርቃል በማለት ገልፀዋል፡፡

## 2.5. የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ

ቋንቋን ለመማር ፍላጎት ና ጉጉት ያለው ተማሪ ዓላማውን ለማሳካት ከጣረ በኋላ በሚማረው ቋንቋ ከፍተኛ ውጤት እንደሚያመጣ እና ቋንቋውንም በተሳካ ሁኔታ መጠቀም እንደሚችል ይታወቃል፡፡ ጋረድነር ና ላምቤርት (1972) የሁለተኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት አይነቶች እያንዳንዳቸው ከቋንቋ ትምህርት ጋር ያለውን ዝምድና በተመለከተ እና ከተነሳሽነት ጋር በተያያዘ ጥናት ካካሄዱት ተመራማሪዎች ውስጥ ቀዳሚ ተመራማሪዎች ናቸው፡፡

ሁለተኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት አይነቶች ከትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ብሮውን (2000) እና ኢሊስ (1994) ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት፣ ውህዳዊና ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት፣ውስጣዊና ውጫዊ ተነሳሽነት ብለው ይመድቡታል፡፡ እነዚህም እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡

### 2.5.1. ጥቅማ ጥቅማዊና ውህዳዊ ተነሳሽነት

ኢሊስ (1994) ዋልፍ (1982) ጠቅሰው ትውልዳቸው የስፔን የሆኑ ተማሪዎች ውህዳዊና በጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነትን የተመለከቱ ጥያቄዎችን ተጠይቀው እነዚህ ተማሪዎች ጥሩ አመለካከት ያሳዩት ለሁለቱም የተነሳሽነት አይነቶች ነው በማለት ገልፀዋል፡፡

ኖኢልስ (2001) ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት መማር ተነሳሽነት አይነቶች ውስጥ ውህዳዊና ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት አይነቶች ውጫዊ ዓላማዎችን ለማሳካት ሲሉ ተማሪዎቹ የሚማሩባቸው የተነሳሽነት አይነቶች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ተጨባጭ የሆኑ ጥቅማ ጥቅሞች ለማግኘት ሲሉ እና ውህዳዊ ተነሳሽነት ደግሞ ከቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር ቅርርብ ወይም ውህደት ለመፍጠር ስለሚማሩ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡

### 2.5.2.ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት

በዚህ ተነሳሽነት አይነት በተደረገው ጥናት ጋርድነርና ላምቤርት የፊሊፒንስ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ችሎታቸው እንዳሳዩ በመግለፅ ይህንን ችሎታቸው እንግሊዝኛ መናገር ከሚችሉ ህዝቦች ማህበራዊነት ለመፍጠር ብለው ሳይሆን በተማሩት ቋንቋ አንዳች ጥቅም ለማግኘት እንደሆነ ብሮውን(200) አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ሁለቱ ተመራማሪዎች ከጥናታቸው

ያገኙትን ግኝት ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ያላቸው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርር ውጤታማ እንደ ሚሆኑ ብሮውን(2000) እና ኢሊስ(1994) ገልጸዋል፡፡

### 2.5.3.ውስጣዊና ውጫዊ ተነሳሽነት

ብሮውን(2000) እንደገለፁት ውጫዊ ና ውስጣዊ ተነሳሽነቶችን ተግባራዊ የሚደረጉት አብዛኛውን ጊዜ የውጪ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ነው እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ውስጣዊ ተነሳሽነት ያላቸው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ውጫዊ ተነሳሽነት ካላቸው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ውጤታማ እንደሚሆኑ ብሮውን (2000) ገልፀዋል፡፡ ምክንያቱም ውስጣዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ለዓላማቸው መሳካት የሚወስኑት መስፈርት ውስጣዊ መስፈርት ስለሆነ እና ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩት ከውስጣቸው በሚመነጭ ፍላጎት እንደሆነ ብሮውን(2000) አስረድተዋል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ተማሪዎች ቋንቋውን የሌላ አካል ድጋፍ ሳያስፈልጋቸው በራሳቸው ተነሳሽነት ቋንቋውን ስለሚማሩት ውጫዊ ተነሳሽነት ካላቸው ተማሪዎች የተሻለ በቋንቋ ትምህርቱ ውጤታማ እነዲሆኑ ያደርጋቸውል፡

## 2.6.የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ተነሳሽነት እና የውጤት ተዛምዶ በተመለከተ ጥናቶችን ተካሂደዋል፡፡ እንዲሁም በዚህ ጥናት የተዳሰሰው በሚቂ እና በአንዘቸ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስረኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች አማርኛን ለመማር ያላቸውን ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ነው፡፡ ስለሆነም ከዚህ ጥናት ጋር ከሚዛመዱ ቀደምት ጥናቶች መካከል በአምስቱ ጥናቶች ላይ ትኩረት በማድረግ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበትን ነጥቦች እንደሚከተለው ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

የመጀመሪያው ተዛማጅ ፅሁፍ እሸቱ (1997) ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በውጤታቸው መካከል ያለ ግንኙነት በሚል ርዕስ ለኤም.ኤ ድግሪ በከፊል ማሟያነት የተካሄደ ጥናት ሲሆን የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ለመማር ባላቸው ፍላጎት ና በትምህርት ባስመዘገቡት ውጤት መካከል ዝምድና መኖር አለመኖሩን ማየት ነው፡፡ ጥናቱ የተከናወነው በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ከሚገኙ አስራ አምስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሶስት ትምህርት ቤቶች ላይ ነው፡፡ትምህርት ቤቶችም በነሲብ ንሞና የተመረጡ ሲሆን የተጠቀመው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የፅሁፍ መጠይቅና ፈተና ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት የሚለየው ጥናቱ ትኩረት ያደረገው ፍላጎት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማስተማር

ሂደት ላይ ያለውን አዎንታዊ ና አሉታዊ ተፅዕኖ ለማየት ና በተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ የመማር ፍላጎት ና ውጤት መካከል ያለውን ግንኙነት ምን እንደሚመስል መመርመር ነው፡፡ የእኔ ጥናት ግን በሚቂ ና በአንዘቾ ትምህርት ቤቶች በጉራጊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ና የትምህርት ውጤት ተዛምዶን መመርመር ነው፡፡ ሌላው ልዩነት የእሽቱ ጥናት ትኩረት ያደረገው ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ፍላጎት ላይ ሲሆን የኔ ጥናት ግን ትኩረት ያደረገው የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነት ላይ ነው፡፡ እንዲሁም ጥናቱ ተጠኚ ተማሪዎች በነሲብ ንሞና ዘዴ መምረጡ ከእኔ ጥናት ጋር እንዲለይ አድርጎታል፡፡  የእሽቱ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የፅሁፍ መጠይቅ ፈተና በመረጃ መሰብሰቢያነት መጠቀሙና የተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ዝንባሌ ከትምህርት ውጤታቸውጋር ያለውን ዝምድና መመርመሩ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

ሁለተኛው ተዛማጅ ፅሁፍ ክፍሌ (2002) አፋቸው በጉሙዝኛ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸው ተነሳሽነትና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ተዛምዶ በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የተካሄደ ጥናት ሲሆን ጥናቱ ዋና ዓላማ የተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን የመማር ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተጠቀማቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የፅሁፍ መጠይቅና ሰነድፍተሻ ሲሆን በጥናቱ ሂደት የተማሪዎቹ ውስጣዊ ተነሳሽነት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ጉልህ ዝምድና እንዳሳየ አመልክቷል፡፡

ይህ ጥናት ከእኔ  ጥናት በሚከተሉት ጉዳዮች ይለያያል፡፡ አንደኛው በክፍሌ ጥናት ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎች አፋቸውን በጉሙዝኛ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ የእኔ ጥናት ተሳታፊ ተማሪዎች ግን አፋቸውን በጉራጊኛ የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ሁለተኛው ልዩነት ጥናቱ የተሰራበት ዓ.ም እና ጥናቱ ከፅሁፍ የጽሁፍ መጠይቅ በተጨማሪ ሰነድ ፍተሻ በመረጃ መሰብሰቢያነት መጠቀሙ ከእኔ ጥናት ጋር ይለያያል፡፡ በተጨማሪም በጥናቱ ሂደት የተማሪዎች ውስጣዊ ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤቱ ጋር ዝምድና በመኖሩ ከዚህ ጥናት ጋር እንዲለይ አድርጎታል፡፡ ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ጥናቱ ይዞት በተነሳው ርእሰ ጉዳይነው፡፡

ሶስተኛው ተዛማጅ ፅሁፍ አበበ (2003) የመሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ና በውጤታቸው መካከል ያለው ዝምድና በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኤም.ኤ ድግሪ መሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን በጥናቱ ክንዋኔ

የተጠቀማቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የፅሁፍ መጠይቅ፣ ቃለ-መጠይቅ ና ምለከታ ናቸው፡፡ ጥናቱ ለማካሄድ ገላጭ የምርምር ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ በጥናቱ ሂደት በተማሪዎች አመለካከት ና በፈተና ውጤታቸው መካከል ዝምድና መኖሩን መረጃው ማመላከቱን ገልፆ መምህራንም ሆነ የቋንቋ ማስተማሪያ መጻሐፍት አዘጋጆች ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የተስማማ የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም ና ማስተማሪያ መጽሐፍት ሲዘጋጁ ይዘት አመራረጥ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ እነደሚያስፈልግ ጠቁሞ ጥናቱ ተደምድሟል፡፡

የአበበ ጥናት ከእኔ ጥናት የሚለየው ጥናቱ የተጠቀመው የመረጃ መሰብሰቢ መሳሪያዎች ከፅሁፍ መጠይቅ በተጨማሪ ቃለ-መጠይቅ ና ምልከታ መሆኑ መሆኑና በጥናቱ ዓላማም የሚለይ መሆኑና ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ ና ዘመን መለያየት ሌላኛው ልዩነት ነው፡፡ ጥናቱ ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የፅሁፍ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት መጠቀሙና ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸውን ዝንባሌ ከትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና መመርመሩ ነው፡፡

አራተኛው ተዛማጅ ፅሁፍ ዘሪቱ (2003) አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የመማር ተነሳሽነት እና የውጤት ተዛምዶ በጋሞኛ ቋንቋ አፈፊት ተማሪዎች በአርባ ምንጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በጋሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን የመማር ተነሳሽነት እና የውጤት ተዛምዶ በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ሲሆን ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመቻቸው መሳሪያዎች የፅሑፍ መጠይቅና ፈተና ናቸው፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ገላጭ መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ተንትናለች፡፡ በጥናቱ ትንተና መሰረት ተማሪዎቹ የመማር ተነሳሽነት ቢኖራቸውም የፈተና ውጤታቸው ግን ከተነሳሽነታቸው ጋር ዝምድና የሌለው መሆኑን ገልፃለች፡፡

የዘሪቱ ጥናት ከዚህ ጥናት የሚለየው ዘሪቱ ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመፈተሽ በፆታና በሁለት የክፍል ደረጃ ያጠናች ሲሆን የእኔ ስራ ደግሞ ያተኮረው ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ በአስረኛ ክፍል ላይ ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ጥናት ከዘሪቱ ጥናት እንዲለይ ያደረገው ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ እና ጊዜ ነው፡፡

ዘሪቱ ጥናት ከዚህ ጥናት ሚለይበት ነጥብ እንዳለው ሁሉ ጥናቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰልበትም ሁኔታ አለ፡፡ ጥናቱ ይዞት የተነሳው ርዕሰ ጉዳይ የእኔ ስራ ይዞት ከተነሳው

ርዕሰ ጉዳይ ጋር ይመሳሰላል፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ የፅሁፍ መጠይቅና ፈተና በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት መጠቀሙ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

አምስተኛው ተዛማጅ ፅሁፍ ተስፋዬ (2014) በሁሩሙና በሶንጣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት ና የውጤት ተዛምዶ በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት ያጠና ሲሆን ጥናቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው አንደኛ ጥናቱ ይዞት የተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛው ጥናቱ የተጠቀማቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የእኔ ጥናት ከተጠቀማቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ጥናቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚለየው በተሰራበት ቦታ እና ዓመተ ምህረት ነው፡፡

ስለዚህ አጥኚዋ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጥናቶች ውስጥ በዚህ ወረዳ እና በእነዚህ ትምህርት ትምህርት ተማሪዎች ላይ የአማርኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ተዛምዶ አስመልክቶ የተሰራ ጥናት ባለመኖሩ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ጥናት አድርጋለች፡፡

# ምዕራፍ ሶስት
# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ምዕራፍ የመረጃ መሰብሰቢያ በሚመለከት የተገለፀበት፣ የናሙና አመራረጥ፣ የጥናቱ የአጠናን ዘዴ፣ ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታና የመረጃ አተናተን ዘዴ በቅደም ተከተል የተገለፀበት ምዕራፍ ነው፡፡

ጥናቱ ተግባራዊ እንዲሆን ገላጭ ተዛምዶዋዊ ዘዴ የተከተለ ነው፡፡ አጥኚዋ ይህንን ዘዴ የተጠቀመችበት ምክንያት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን ተነሳሽነት ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ ለማወቅ ስለሚያመች ነው፡፡

### 3.1.1 የናሙና አመራረጥ

በሚቂና በአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የጉራጊኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን ቋንቋ የመማር ያላቸው ተነሳሽነት እና በትምህርት ውጤታቸው መካከል ያለውን ዝምድና መፈተሽ የጥናቱ ዋና ዓላማ ሲሆን ለዚህ ኣላማም በእኖር ኤነር መገር ወረዳ ከሚገኙ ስድስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሁለት ትምህርት ቤቶች ማለትም የሚቂና የአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች ለጥናቱ የተመረጡበት ምክንያት አንደኛ ደረጃ ከሚማሩ ተማሪዎች የተሻለ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡

ከስድስቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚቂና የአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተመረጠበት ምክንያት አጥኚዋ በሚቂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ለተከታታይ አምስት አመታት በመምህርነት ሙያ እያገለገለች ስለምትገኝ እና አንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም ለሚቂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በጣም ቅርብ ስለሆነ፣ የስድስቱም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋነት የሚጠቀሙበት በመሆኑ ስለሚመሳሰሉ እና ጊዜ ለመቆጠብ እና አጥኚዋ ከስራዋ ጋር የተመቻቹ በመሆናቸው ሚቂና አንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመምረጥ ችላለች፡፡ በተጨማሪም ከጥናቱ ዓላማ አንፃር በቂ መረጃ ለማግኘት የሚቻልበትን ግምት ታሳቢ በማድረግ እነዚህ ሁለቱ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል፡፡ በ2015 ዓ.ም አስረኛ ክፍል የሚማሩ የጉራጊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች

በዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ በመምረጥ የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት ተማሪዎቹ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ስለሚማሩ በሚቀጥለው ክፍል ደረጃ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ይችሉ ዘንድ ጠቃሚ መረጃ ከጥናቱ ሊገኝ ይችላል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

ያለው (1996፡)‘ ’ተመራማሪው ከሁሉም በፊት የጥናቱ ተጠኚዎች ማወቅ እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡ ይህ ሲባል ተጠኚው ተመራማሪውን የሚፈልገውን መረጃ ሊሰጡት ይችላሉ? መረጃው አለቸው? የሚጠይቃቸው ጥያቄዎች ሁሉ በተመለከተ አስመልክቶ አጥጋቢ እውቀትና የሂይወት ገጠመኝ አላቸው? የሚሉ የመሳሰሉት ጥያቄዎችን ከመለሱ“ እነዚህ ተጠኚዎች በቂ መረጃ እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ከጥናቱ በፊት በተካሀደው ቅኝት ለጥናቱ በተመረጠው የክፍል ደረጃ በ2015 ዓ.ም በሚቂ ሁለተኛ ደረጃ 27 እና 26 ተማሪዎችን የያዙ ሁለት የአስረኛ ክፍሎችና በአንዘች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ 26፣26 ተማሪዎችን የያዙ ሁለት ክፍሎች እንዳሉ ተስተውሏል፡፡

በተጠቀሱት የክፍል ደረጃ ያሉት ተማሪዎች ብዛት 105(መቶ አምስት) ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ በሚቂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙት ተማሪዎች 24 (ሃያ አራት) ወንድ እና 29 (ሃያ ዘጠኝ) ሴት በድምሩ 53 (ሃምሳ ሶስት) ተማሪዎች ሲሆኑ በአንዘች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ ተማሪዎች 25 (ሃያ አምስት) ወንድ እና 27 (ሃያ ሰባት) ሴት በድምሩ 52(ሃምሳ ሁለት) ተጠኚዎች ሲሆኑ፡፡ በአጠቃላይ በጥናቱ የታቀፉት የሁለቱ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ብዛት 49 (አርባ ዘጠኝ ) ወንድ እና 56 (ሃምሳ ስድስት) ሴት ተማሪዎች በድምሩ 105 (መቶ አምስት) ተማሪዎች ሆኗል፡፡ ስለዚህ ተጠኚ ተማሪዎች በእድል ሰጭ የናሙና ዘዴ በመምረጥ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት 80% በመውሰድ የተዘጋጀው የፅሁፍ መጠይቅ በማስሞላ እና የችሎታ መለኪያ ፈተና በመፈተን በናሙና ምንጭነት አገልግለዋል፡፡

### 3.1.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በጉራጌ ዞን በእኖር ኤነር መገር ወረዳ ከሚገኙ በሚቂ እና በአንዘቸ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም አስረኛ ክፍል ሲማሩ የነበሩ 105 (መቶ አምስት) ተማሪዎች አጥኚዋ ካጋጠሟት ችግሮች አንፃር ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ማለትም ከሚቂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 53 ተማሪዎች 42 ተማሪዎችን 21 ወንድና 21 ሴት ተማሪዎችን፣ ከአንዘቸ ሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤት ደግሞ 52 ተማሪዎች ውስጥ 41 ተማሪዎችን 20 ወንድና 21 ሴት ተማሪዎች እና በጠቅላላው ከሚቂና

ከአንዘቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በድምሩ 83 ተማሪዎች ተመርጧል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 41 ወንድና 42 ሴት ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከሚቂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 42 ተማሪዎች የጠቅላላውን(53) ተማሪዎች 80%ና ከአንዘቻ ትምህርት ቤት 41 ተማሪዎች የጠቅላላውን (52) ተማሪዎች 80% የሚይዙ ስለሆኑ አማካይ ውክልና እንዲኖራቸው በመተማመን በናሙናነት መመረጥ እንደሚገባቸው በመወሰን በቁጥር 83 የሆኑ ተማሪዎችን ከሁለቱም ትምህርት ቤት በፆታ ከተለዩ በኋላ በዕድል ሰጭ ናሙና ዘዴ በመጠቀም ተመርጧል፡፡ የተሳታፊዎቹ ማንነትና ያሉበት ክፍልም ተለይቶ በየትምህርት ቤታቸው ሆነው መረጃውን እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ አጥኚዋ ለናሙና እድል ሰጭ የተጠቀመችበት ምክንያት መረጃ በሚሰበሰብባቸው መማሪያ ክፍሎች ውስጥ እያንዳንዱ አባል በእኩል ደረጃ የመምረጥ ዕድል ስለሚሰጥ ወይም በአንድ ጥናት ሊካተቱ የሚችሉባቸው ናሙናዎች ብዙሀኑን እንደሚወክሉ ለማድረግ ስለሚያገለግል ነው፡፡

ያለው (1996) በእድል ሰጭ የናሙና ዘዴ እያንዳንዱ የጥናቱ አካላይ አባል ለጥናቱ ናሙና ሆኖ ለመመረጥ የተወሰነ እድል አለው፡፡ በእርግጥ እድሉ ይህን ያህል ነው በሎ መናገር አይቻልም፡፡ ተመራማሪው ለመጠቀም እንደሚወስነውና እንደሚያስፈልገው የናሙና ሂደት ይለያያል፡፡ በእድል ሰጭ የናሙና ዘዴ ተመራማሪው ሳይንሳዊ ዘዴንና ሎጂክ መሰረት አድርጎ የጥናቱ አካላይ ባህሪይ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን ይመርጣል፡፡ በዚህ ወቅት የግሉን የግምገማ ሂደት አይከተልም፡፡

ከሚቂ ትምህርት ቤት ከተመረጡት 42(አርባ ሁለት) ተማሪዎች 2(ሁለት) ተማሪዎች እና ከአንዘቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ከተመረጡት 41 ተማሪዎች 1(አንድ) ተማሪ መጠይቁን በተሰጠው መመሪያ መሰረት በትክክል ባለመሙላታቸው የተበላሸ ተብሎ ተይዟል፡፡ በዚህ ምክንያት ጥናቱ ከሚቂ ትምህርት ቤት በ40 (በአርባ) ተማሪዎች እንዲሁም ከአንዘቻ ትምህርት ቤት በ40 (በአርባ) ተማሪዎች ላይ ተሂዷል፡፡

በአጠቃላይ ከሁለቱም ትምህርት ቤት ከተመረጡት 83(ሰማኒያ ሶስት) ተማሪዎች ውስጥ 3(ሶስቱ) ከጥናቱ ውጪ ሆነው ከሁለቱ ትምህርት ቤቶች በ80 (ሰማኒያ) ተማሪዎች ላይ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ከሚቂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስረኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ 20(ሃያ) ወንድና 20(ሴት) እንዲሁም ከአንዘቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስረኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ 20(ሃያ) ወንድና 20(ሴት) ተማሪዎች ሲሆኑ ከሁለቱም ትምህርት ቤቶች በጠቅላላው 40(አርባ) ወንድ ና 40(አርባ ) ሴት ተማሪዎች ላይ ጥናቱ ሊካሄድ ችሏል፡፡

### 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የተነሳበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ትምህርት ቤቶችና ተማሪዎች ከተመረጡ በኋላ አጋዥ ይሆናሉ ተብሎ የተመረጡት የፅሁፍ መጠይቅና ፈተና በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ተመርጠዋል። የጽሁፍ መጠይቆቹ የተነሳሽነት አይነትና መጠን የሚያመለክቱ ሲሆኑ የአማርኛን ቋንቋ ትምህርት ፈተና ደግሞ የተጠኚዎቹ የትምህርት ውጤት ያሳያል።

#### 3.2.1 የፅሁፍ መጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቅ በትምህርት፣ በሶሻል ሳይንስ፣ በጤና፣ በፖለቲካ ሳይንስ፣ በስነባህሪና በሌሎች በርካታ የምርምር መስኮች ምናልባት ከሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የበለጠ ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ያለው የፅሁፍ መጠይቅ ነው **ያለው እንዳወቀ** (1996)። በመሆኑም አጥኚዋ ጥናታዊ ፅሁፉን ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ መጠይቆችን በማዘጋጀት ተሳታፊ የሆኑ ለሚቄና ለአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል 80(ሰማኒያ) ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የመማር ተነሳሽነት ያላቸው መሆኑና አለመሆኑ እንዲሁም በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል ያለው አማርኛ ቋንቋን የመማር ተነሳሽነት ልዩነት ለማረጋገጥ ያስችላል ብላ በማመን የፅሁፍ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት መርጣ ተጠቅማለች። የመጠይቁ ዓላማ ለተጠኚ ተማሪዎች ከተገለፀላቸው በኋላ መጠይቆችን ለተማሪዎች በማሰራጨት ለጥያቄዎቹ መልስ በነፃነት እንዲመልሱ ተደረጓል።

የፅሁፍ መጠይቅ ለጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጠበት ምክንያት ያለው እንዳወቀ (1996) የፅሁፍ መጠይቅ ከሌሎቹ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጋር ሲወዳደር ጊዜን፣ ጉልበትንና ገንዘብን ይቆጥባል፤ የመላሾችን ማንነት ስለማይገልፅ መላሾች አስተማማኝ መረጃ እንዲሰጡ ስለሚያበረታታ እና ለሁሉም ተጠኚዎች አንድ አይነት ጥያቄ በማቅረብ ከጥያቄ አቀራረብ ልዩነት የተነሳ የሀሳብ ልዩነት እንዳይፈጠር ያደርጋል በማለት ገልፀዋል። በመሆኑም የፅሁፍ መጠይቅ ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ተመርጧል። ለተጠኚዎችም የቀረበው ጥያቄ አይነት ዝግ ጥያቄ ሲሆኑ መጠይቆችም ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ግንኙነት ያላቸው ናቸው።

የፅሁፍ መጠይቁ 38 ጥያቄዎች የያዘ ሲሆን የመጠይቁ ዝግጅት ደግሞ ጋርደነር (2004) ከተጠቀሟቸው ጥያቄዎች ለጥናቱ በሚያመች መልኩ ማሻሽያ ተደርጎ ወደ አማርኛ ተተርጉመዋል።

መጠይቁም አስራ አምስት ውስጣዊ ተነሳሽነት፣ ዘጠኝ ውጫዊ ተነሳሽነት፣ ስድስት ውህዳዊ ተነሳሽነት እና ስምንት ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነትን እንዲለኩ ተደርገው የተዘጋጁ ሲሆን ውስጣዊ ተነሳሽነትን የሚመለክቱ ጥያቄ ቁጥሮች አንደኛ፣ አምስተኛ፣ አስራ ሶስተኛ፣ አስራ አራተኛ፣ አስራ ስድስተኛ፣ አስራ ዘጠነኛ፣ ሀያ ሶስተኛ፣ ሀያ አራተኛ፣ ሀያ አምስተኛ፣ ሀያ ሰባተኛ፣ ሀያ ዘጠነኛ፣ ሰላሳ አንደኛ፣ ሰላሳ ሶስተኛ፣ ሰላሳ አራተኛ እና ሰላሳ ሰባተኛ ሲሆኑ ውጫዊ ተነሳሽነት የሚያመለክቱ ጥያቄ ቁጥሮች ደግሞ ሁለተኛ፣ ስድስተኛ፣ ዘጠነኛ፣ ሀያኛ፣ ሀያ ሁለተኛ፣ ሀያ ስምተኛ፣ ሰላሳኛ፣ ሰላሳ አምስተኛ እና ሰላሳ ስምተኛ ናቸው። እንዲሁም ሶስተኛ፣ አራተኛ፣ አስረኛ፣ አስራ አንደኛ፣ ሀያ ስድስኛ እና ሰላሳ ሁለተኛ ውህዳዊ ተነሳሽነት የሚያመለክቱ ጥያቄ ቁጥሮች ሲሆኑ ሰባተኛ፣ ስምተኛ፣ አስራ ሁለተኛ፣ አስራ አምስተኛ፣ አስራ ሰባተኛ፣ አስራ ስምተኛ፣ ሀያ አንደኛ እና ሰላሳ ስድስተኛ ደግሞ ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት የሚያመለክቱ ጥያቄ ቁጥሮች ናቸው። ተማሪዎች መጠይቁን ሲሞሉ አሞላሉን እንዳያበላሹት ጥያቄዎቹን በሰንጠረዥ ቀርበዋል።

ከመጠይቆችም ውስጥ ‹‹በአማርኛ መምህሬ ታርመው የተመለሱ የቤት ስራዎቼ ስህተቶችን ለማረም አልጨነቅም›› የሚለው አስራ ስድስተኛ ጥያቄ አሉታዊ ስለሆነ የጥያቄው መልስ ውጤት በተቃራኒ ኮድ ተይዟል። ‹‹አማርኛ ለመማር ፍላጎት የለኝም›› አስራ ዘጠነኛ ጥያቄ፣ እና ‹‹አማርኛ መማር ፍላጎቱ ስለሌለኝ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ሳጠናቅቅ አማርኛ መማር አቆማለሁ›› ሚለው 33ኛ ጥያቄ እንዲሁም ‹‹አማርኛ መማር ጊዜ መግደል ነው›› ለሚለው ሀያ ሰባተኛ ጥያቄዎች የመልሳቸው ውጤት በተቃራኒ ኮድ ተይዟል። ምክንያቱም ተጠኚዎቹ ለጥያቄዎቹ የሚሰጡትን ምላሽ አዎንታዊ ከሆነ ተነሳሽነት እንደሌላቸው ሲያመለክት ለጥያቄው አሉታዊ መልስ ከሰጡት ደግሞ ተነሳሽነት እንዳለቸው ስለሚያመለክት ነው።

መጠይቆችም ለተጠኚ ተማሪዎች ከመበተናቸው በፊት በጥናቱ አማካሪ ታይተዋል። ከዚያም በስራ ባልደረቦቼ ተገምግሞ የጥያቄዎቹ ትክክለኛነት ለመፈተሽ የሁለቱም ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን በማስፈቀድ ከሁለቱም ትምህርት ቤት በ14 ወንድ እና በ16 ሴት ተማሪዎች በጠቅላላው በ30 የ11ኛ ክፍል የጉራጊኛ ቋንቋ አፋቸውን በፈቱ ተማሪዎችን ተወስደው የሙከራ ጥናት በማድረግ በሙከራ ጥናቱ ከተማሪዎች የተነሱ አንዳንድ ጥያቄዎች ማስተካከያ ከተደረገ በኋላ ወደ ዋናው መረጃ አሰባሰብ ሂደት ተገብቷል።

የጥናቱ መረጃ ለማሰባሰብ ከሚቂና ከአንዘቸ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም ሌሎችም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ከሚቂ ሁለተኛ ደረጃ

የተመረጡ ተጠኚ ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ከሚገኘው አይሲቲ ክፍል እንዲገቡ በማድረግና ከአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተመረጡ ተጠኚ ተማሪዎች ደግሞ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ከሚገኘው በአንድ የተማሪዎች ቤተ-መጽሕፍት ውስጥ ገብተው መጠይቁ ላይ ቅደም ተከተላቸው የጠበቀ ኮድ በመስጠት ተጠኚ ተማሪዎች የየራሳቸው ስሜት፣ አመለካከትና ውሳኔ ብቻ የሚወክሉ አማራጮችን እንዲመርጡ በየትምህርት ቤቶቹ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ማብራሪያ ከተሰጣቸው በኋላ መጠይቁ ሁለቱም ትምህርት ቤቶች በተመሳሳይ ቀንና በተመሳሳይ ሰዓት በሰላም ሞልተው አጠናቋል፡፡

### 3.2.2 የችሎታ መለኪያ ፈተና

አጥኚዋ ከፅሁፍ መጠይቅ ቀጥሎ የችሎታ መለኪያ ፈተና በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ተጠቅማለች፡፡ ተማሪዎችን የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱት ለማወቅ መምህራን በሚያስተምሩት የትምህርት አይነት ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልኩ ፈተና አዘጋጅተው ተማሪዎቻቸውን የመግምገም ወይም የመፈተን ሀላፊነት አለባቸው፡፡ በመሆኑም ትምህርትና ፈተና የማይለያዩ ጉዳዮች ስለሆኑ የጠበቀ ግንኙነት አላቸው፡፡

ያለው (1996) ‹‹ፈተና ማለት  ጥያቄዎች ተዘጋጅተው በአንድ አይነት ሁኔታ የተፈታኞች አእምሮአዊና ስነ-ባህሪያዊ  በተመለከተ መረጃዎችን የሚሰበሰብበት መሳሪያ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በአንድ አይነት ሁኔታ ስንል ፈተናው ለተጠኚዎቹ የሚሰጠው በ በተመሳሳይ ጊዜ፣ አፈታተንና የአተራረም ሁኔታእንዲሁም ተመሳሳይ የመልስ አሰጣጥ መልክና መመሪያ እና ከተቻለም በተመሳሳይ ፈታኝ ወይም ተቀራራቢ የአፈታተን ብቃት ባላቸው ሰዎች የሚካሄድ መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡›› ነው በማለት ያበራራሉ፡፡ አጥኚዋ ከተማሪዎች ውጤት ማጠራቀሚያ ላይ ካለው ውጤት የተሻለ ታአማኒነት ያለው ፈተና መሆኑን ስለአመነች የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ችሎታ ውጤት ለማግኘት ፈተናን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅማለች፡፡

አጥኚዋ ፈተናው ከማዘጋጀቷ በፊት በአስረኛ ክፍል የተማሪ መማሪያ መፅሕፍት ላይ  የሚገኙ ይዘቶች ተማሪዎች የተማሩትን አስረኛ ክፍል ከሚያስተምሩ የሁለቱም ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ  መምህራን በመጠየቅና በማየት ከሁለቱም ትምህርት ቤት የተማሪዎች የአማርኛ መማሪያ ደብተርና የመማሪያ መፅሕፍት የይዘት ግንኙነት በማመሳከር ለይታለች፡፡ ከዚያም በኋላ ከሁለቱም ትምህርት ቤት  በተለመደው የፈተና አይነት ከሁለቱም ክሂሎች ውጪ ማለትም ከመናገርና ከማዳመጥ ክሂል ውጪ ያሉትን ክሂሎች ያካተተ ፈተና አዘጋጅታለች፡፡

በሁለቱም ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምህራን የፈተናው ጥያቄዎች አወጣጥ የቋንቋ ፈተና ባህሪያት ማሟላት አለማሟላቱን ተገምግሞና በጥናቱ አማካሪ ታይቶ አስፈላጊውን ማስተካከያ ከተደረገ በኋላ ቀደም ሲል ከሁለቱም ትምህርት ቤት ተወጣጥተው መጠይቁ የሞሉ 30 የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ፍቃደኝነታቸው ተረጋግጦ የሙከራ ጥናት ተደርጓል፡፡

በሙከራ ጥናቱ በፈተናው ጥያቄዎች ዙሪያ የታዩ ጉደለቶችን በማስተካከል ከተጠኚዎች ጋር በተቀጣጠርነው መሰረት በቀጠሮ ቀን በመገናኘት  በፅሁፍ መጠይቁ ላይ በተሞላላቸው ኮድ መሰረት በፈተናው ላይ በጥንቃቄ በተመሳሳይ  ተሞልቶ በቅደም ተከተላቸው  ከተሰጣቸው በኋላ ፈተናው የሁለቱም ትምህርት ቤቶች በተመሳሳይ ቀንና በተመሳሳይ ሰዓት ተጠናቶ መረጃው ተሰብስቧል፡፡

### 3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

የተሰበሰቡት መረጃዎች መልሶቻቸው በትክክል መሞላታቸውን ከተረጋገጠ በኋላ  ለመተንተን እንዲመች ኮድ ተደርጎ በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ ላይ በማስፈር መረጃው በደንብ ከተጣራ በኋላ ትንተና ተደርጓል፡፡

የተጠኚዎችን ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ማወቅ እንዲቻል በቀረቡት የጥናቱ መነሻ መጠይቆች መሰረት የተሰበሰቡን መረጃዎች (SPSS application) በገላጭ እስታቲክስ ምን እንደሚመስሉ ለማብራራት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የፒርሰን የተዛምዶ (pearson correlation) መወሰኛ በተለዋዋጮች መካከል ያለውን ዝምድና ለማረጋገጥ ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ በተጨማሪም በሚቴና በአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን አማካይ የአማርኛ ቋንቋን መማር ተነሳሽነት ልዩነት ለማወቅ የነጠላ ናሙና ፍተሻ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

# ምእራፍ አራት

# የመረጃ ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ ከተጠኚዎች የተገኙትን አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከሚለኩ መጠይቆች ውጤቶችን በመተንተኛ ዘዴዎች በመተንተን የተገኙትን ውጤቶች በማብራራት በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

## 4.1 የመረጃ ውጤት ትንተና

በጥናቱ እንደተገለፀው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በሁለተኛ ቋንቋነት የመማር ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ፈትሾ ውጤቱን ለማየት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ በሰንጠረዥ ከተገለፀ በኋላ በ50 የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥያቄዎች በያዘ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና የተገኘው የትምህርት ውጤት እና በ38 የፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ በምዕራፍ አንድ ላይ የተቀመጡትን የጥናቱ መሰረታ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

### 4.1.1 የተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ

**ሰንጠረዥ አንድ፡**

| | | | ትምህርት ቤት | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሚቂ | አንዘቸ | |
| ፆታ | ወንድ | ብዛት | 20 | 20 | 40 |
| | | ፐርሰንት | 25.0% | 25.0% | 50.0% |
| | ሴት | ብዛት | 20 | 20 | 40 |
| | | ፐርሰንት | 25.0% | 25.0% | 50.0% |
| ድምር | | ብዛት | 40 | 40 | 80 |
| | | ፐርሰንት | 50.0% | 50.0% | 100.0% |

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ እንደተገለፀው የተጠኚዎች መረጃን በተመለከተ ከሚቂ ትምህርት ቤት 20 (25.0%) ሴት ተማሪዎች ፣ ከአንዘቸ ደግሞ 20 (25.0%) ሲሆን በአጠቃላይ ከሁለተም ትምህርት ቤቶች 40 (50.0%) ሴቶች እና ወንድ ተማሪዎች 20 (25.0%) ከሚቂ ትምህርት ቤት፣ 20 (25.0%) ከአንዘቸ ትምህርት ቤት ሲሆን በድምሩ 40 (50.0%) ወንዶች በጥናቱ ተሳትፈዋል፡፡

### 4.1.2 የ ሁለቱም ትምህርት ቤቶች የፈተና ውጤት

**ሰንጠረዥ ሁለት፡**

| ትምህርት ቤት | ብዛት | አማካይ ፈተናውጤት | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| ሚቂ | 40 | 53.33 | 13.43 |
| አንዘቾ | 40 | 46.87 | 14.39 |
| ድምር | 80 | 50.10 | 14.20 |

በሰንጠረዥ 2፡ እንደተመለከትነው በሁለቱምትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና የሚከተለው ይመስላል፡፡

የሚቂ አስረኛ ክፍል ተማሪዎች አማካይ የፈተና ውጤት 53.33 ሲሆን 13.43 መደበኛ ልይይት ነው፡፡ የአንዘቾ አስረኛ ክፍል ተማሪዎች አማካይ ውጤት 46.87 ሲሆን 14.39 መደበኛ ልይይቱ ነው፡፡ እንዲሁም የሚቂና የአንዘቾ ተማሪዎች 50.10 አጠቃላይ የፈተና ውጤት ሲሆን 14.20 መደበኛ ልይይት ነው፡፡

### 4.1.3 የተነሳሽነት አይነቶች ውጤት በገላጭ እስታቲስቲክስ

**ሰንጠረዥ ሶስት፡**

| | ብዛት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|
| ውስጣዊ | 80 | 3.54 | .49 | .24 |
| ጥቅማ ጥቅማዊ | 80 | 3.11 | .60 | .36 |
| ውህዳዊ | 80 | 3.08 | .57 | .33 |
| ውጫዊ | 80 | 2.96 | .56 | .31 |

በሰንጠረዥ 3 ላይ እንደተመለከትነው የተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት በእያንዳንዱ የተነሳሽነት አይነቶች ሲታይ የሚከተለው ይመስላል፡፡

የሁለቱም ትምህርት ቤት አጠቃላይ የተማሪዎች ውስጣዊ ተነሳሽነት ውጤታቸው 3.54 ሲሆን 0.49 መደበኛልይይት ነው፤ 3.11 የጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት ሲሆን 0.60 መደበኛ ልይይት ነው፤ 3.08 የውህዳዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት ሲሆን 0.57 መደበኛ

ልይይትነው፤ 2.96 ውጫዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት ሲሆን 0.56 መደበኛ ልይይት ነው። ይህ ትንተና የሚያመለክተው ተማሪዎች የተሻለ የተነሳሽነት ውጤት ያሳዩት በውስጣዊ ተነሳሽነት ላይ ሲሆን ቀጥሎ በጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ነው። ስለሆነም የተማሪዎቹ ውጤት ከውስጣዊ ተነሳሽነት ቀጥሎ ጎልቶ የሚታየው በጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ላይ መሆኑን ተረጋግጧል።

ይህም የሚያሳየው የጉራጊኛ አፊ-ፊት የሆኑ የሚቁና የአንዘቻ አሰረኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን ቋንቋ ትምህርት የ በአብዛኛው የሚከታተሉበትየተነሳሽነት ደረጃ በውስጣዊ ተነሳሽነት ከዚህ ሲቀጥል ደግሞ በጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ደረጃ መነሳሳት እንደሚታይባቸው ያመለክታል። ይህም በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለፀው ብሮውን (2000) ውስጣዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ውጤታማ እንደሚሆኑ ገልፀዋል። ከዚህ ሀሳብ በመነሳት የጉራጊኛ አፊ-ፊት የሆኑ የሚቁና የአንዘቻ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸውን የሚከታተሉት በአብዛኛው በውስጣዊ ተነሳሽነት ስለሆነ በቋንቋ ትምህርታቸው ውጤታማ ይሆናሉ።

### 4.1.4 የሁለቱም ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተነሳሽነትና የውጤት ተዛምዶ

**ሰንጠረዥ አራት፡**

| | | የፊና ውጤት | ውስጣዊ | ውጫዊ | ውህዳዊ | ጥቅማ ጥቅማዊ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የፊተና ውጤት | የፒርሰን ተዛምዶ | 1 | | | | |
| | የፒ ዋጋ | | | | | |
| ውስጣዊ | የፒርሰን ተዛምዶ | .49 | 1 | | | |
| | የፒ ዋጋ | .669 | | | | |
| ውጫዊ | የፒርሰን ተዛምዶ | .084 | .208 | 1 | | |
| | የፒ ዋጋ | .461 | .064 | | | |
| ውህዳዊ | የፒርሰን ተዛምዶ | .421** | .084 | .226* | 1 | |
| | የፒ ዋጋ | .000 | .459 | .044 | | |
| ጥቅማ ጥቅማዊ | የፒርሰን ተዛምዶ | .147 | .163 | .515** | .326** | 1 |
| | የፒ ዋጋ | .193 | .148 | .002 | .003 | |

ከላይ በሰንጠረዥ አራት ላይ እንደምናየው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የመማር ተነሳሽነትና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ ደረጃ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተቀምጧል። ተነሳሽነትና

የትምህርት ውጤት ዝምደና እንዳላቸው የሚታወቀው ውጤት በኔጋቲቭ አንድና በፖዘቲቭ አንድ መካከል ሲመጣ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ የፒ ዋጋ ከ0.05 በታች ከሆነ ተለዋዋጮቹ ዝምድና አላቸው ማለት ሲሆን ከ0.05 ከበለጠ ተለዋዋጮቹ ዝምድና የላቸውም፡፡ በዚህ መሰረት በሰንጠረዥ አምስት ላይ እያንዳንዱ የተነሳሽነት አይነቶች የ ከትምህርት ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

አንደኛው ውስጣዊ ተነሳሽነት እና የ የአማርኛ ትምህርት ውጤት በፒርሰን ተዛምዶ ሲታይ ዝምድና የላቸውም፡፡ የፒርሰን ተዛምዶ ዋጋው 0.49 ቢሆንም የፒ ዋጋ 0.669 ስለሆነ የፒ ዋጋ 0.05 % በላይ በመሆኑ ዝምድና የለውም፡፡

ሁለተኛው ውጫዊ ተነሳሽነት እና የትምህርት ውጤት በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ሲታይ ዝምድና የላቸውም፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳን ውጫዊ ተነሳሽነት ና የትምህር ውጤት 0.084 ቢሆንም የፒ ዋጋ 0.461 ስለሆነ ነው፡፡

ሶስተኛው ውህዳዊ ተነሳሽነትና የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ሲታይ ዝምድና አላቸው፡፡ ምክንያቱም ውህዳዊ ተነሳሽነትና የፈተና ውጤት 0.421 ከመሆኑም በላይ የፒ ዋጋ 0.000 በመሆኑ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ዝምድናው ጉልህ መሆኑን ነው፡፡

አራተኛው ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት እና የትምህርት ውጤት በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ሲታይ ዝምድና የላቸውም፡፡ ምክንያቱም ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት እና የፈተና ውጤት 0.147 ሲሆን የፒ ዋጋ ደግሞ 0.193 ስለሆነ ነው፡፡

ሌላው የአማርኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት አይነቶች ከእርስ በርሳቸው ጋር ያላቸው ዝምድና በተመለከተ ከላይ በሰንጠረዥ 5፡ ላይ እንደታየው የተማሪዎች ውስጣዊ ተነሳሽነት ከየትኞችም የቋንቋ መማር ተነሳሽነት አይነቶች ጋር ዝምድና የለውም፡፡ ነገር ግን ውጫዊ ተነሳሽነት ከውህዳዊ ተነሳሽነት ጋር ሲታይ በመካከላቸው ዝምድና አለ፡፡ ምክንያቱም የፒርሰን ተዛምዶ ውጤት 0.226 ከመሆኑም በላይ የፒ ዋጋ 0.044 ስለሆነ ነው፡፡ በተመሳሳይ ውጫዊ ተነሳሽነት ከጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ጋር ከፍተኛ ግንኙነት(ዝምድና) አለው፡፡ ይህም የተረጋገጠው የፒርሰን ተዛምዶ ውጤት 0.515 በመሆኑ ወይም የፒ ዋጋ 0.000በመሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም ውህዳዊ ተነሳሽነት ከጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ጋር ሲታይ በሁለቱም መካከል ዝምድና አለ፡፡ ዝምድና መኖሩን የታወቀው የፒርሰን ተዛምዶ ዋጋ 0.326 ከመሆኑም ጋር የፒ ዋጋ 0.003 በመሆኑ ነው፡፡

### 4.1.5 በሚቂና በአንዘቻ ትምህርት ቤቶች መካከል ያለው አማካይ አማርኛ የመማር ተነሳሽነት ውጤት

**ሰንጠረዥ አምስት፡**

| ተለዋዋጭ | ሚቂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | | አንዘቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | | የቲ-ዋጋ | የp-ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | | |
| ውስጣዊ ተነሳሽነት | 3.5054 | .49682 | 3.5696 | .48915 | .583 | .561 |
| ውጫዊ ተነሳሽነት | 3.0031 | .5919 | 2.9187 | .58940 | .674 | .503 |
| ውህዳዊ ተነሳሽነት | 3.1965 | .57382 | 2.9665 | .55375 | -1.824 | .072 |
| ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት | 3.0000 | .48569 | 3.2225 | .69115 | 1.666 | .100 |

ከላይ ሰንጠረዥ ሰባት ላይ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች መካከል ያለው የአማርኛ መማር ተነሳሽነት አይነቶች አማካይ ውጤት ተቀምጧል፡፡ በሰንጠረዡ የተቀመጠው መረጃ እንደሚያሳየው የሚቂ ተማሪዎች ውስጣዊ ተነሳሽነት በተመለከት 3.5054 አማካይ ውጤት ሲሆን 0.49682 መደበኛ ልይይት ነው፤ የአንዘቻ ትምህርት ቤት ተማሪዎች 3.5696 አማካይ ውጤት ና መደበኛ ልይይት 0.48915 ሲሆን ልዩነት በቲ-ስታቲክስ ሲታይ የቲ ዋጋ 0.583 እና የp ዋጋ 0.561 ነው፡፡ ስለዚህ የp ዋጋ ከ0.05% በላይ በመሆኑ ትምህርት ቤቶቹ መካከል በተማሪዎች ውስጣዊ ተነሳሽነት ልዩነት የለም፡፡

ሁለተኛው ውጫዊ ተነሳሽነትን በሚመለከት የሚቂ ተማሪዎች 3.0031 አማካይ ውጤት ሲሆን 0.5919 መደበኛ ልይይት ነው፡፡ የአንዘቻ ተማሪዎች 2.9187 አማካይ ውጤታቸው ሲሆን 0.58940 መደበኛ ልይትት ነው፡፡ይህን ልዩነት በቲ-ስታቲክስ ሲታይ የቲ ዋጋ 0.674 እና የፒ ዋጋ 0.53 መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረት የp ዋጋ ከ0.05% በላይ ስለሆነ በሁለቱም ትምህርት በቤቶች የጎላ ልዩነት የለም፡፡

ሶስተኛው ውህዳዊ ተነሳሽነት በተመለከተ የሚቂ ተማሪዎች ውህዳዊ ተነሳሽነት 3.1965 አማካይ ውጤት ሲሆን እና 0.57382 መደበኛ ልይይት ነው፡፡ ሲሆን የአንዘቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ውህዳዊ ተነሳሽነት ውጤት 2.9665 እና መደበኛ ልይይት 0.55375 ሲሆን ይህ

ልዩነት በቲ-ስታቲክስ ሲታይ የቲ- ዋጋ -1.824 እና የፒ ዋጋ 0.072 ነው፡፡ ስለዚህ የp ዋጋ ከ0.05% በላይ በመሆኑ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች መካከል የጎላ ልዩነት የለም፡፡

አራተኛው ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ሲሆን የሚቄ ተማሪዎች ውጤት 3.0000 አማካይ ውጤት ሲሆን 0.48569 መደበኛ ልይይት ነው፡፡ የአንዘቾ ተማሪዎች 3.2225 አማካይ ውጤት ሲሆን እና መደበኛ ልይይት 0.69115 መደበኛ ልይይት ነው፡፡ ሲሆን ይህ ልዩነት በቲ - ስታቲሲክስ ሲታይ የቲ ዋጋ 1.666 እና የp ዋጋ 0.100 መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረት የp ዋጋ ከ0.05% በላይ ስለሆነ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የጎላ ልዩነት የለም፡፡

በአጠቃላይ ትንተናው እንደሚያመለክተ በውስጣዊ ተነሳሽነት፣ በውጫዊ ተነሳሽነት፣ በውህዳዊ ተነሳሽነትና በጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነቶች መካከል ልዩነት አልታየም፡፡

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

በዚህ ጥናት በጉራጊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የሚቄና የአንዘቾ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትና በትምህርት ፈተና ውጤት መካከል የታየው ዝምድና አጥኚዋ ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት በተጠቀመቻቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች ከዚህ በላይ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ በጥናቱ ትንተና መሰረት የጥናቱ ውጤት የጥናቱ መሰረታዊ ጥቄዎች መነሻ በማድረግ እንደሚከተለው እንደሚከተለው ተገልፀዋል፡፡

### 4.2.1 በሚቄና በአንዘቾ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጉራጊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በእያንዳንዱ ተነሳሽነት ያላቸው ተነሳሽነት ምን ያህል ነው?

የተማሪዎቹ አማርኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ምን ያህል እንደሆነ ለማረጋገጥ በሰንጠረዥ 4 ላይ ከጽሑፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሰረት የተማሪዎቹ አማርኛ የመማር ተነሳሽነት አማካይ ውጤት በደረጃ ቅደም ተከተል የውስጣዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.54 መደበኛ ልይይት 0.49፣ የጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.11 መደበኛ ልይይት 0.60፣ የውህዳዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.08 መደበኛ ልይይት 0.57 እና የውጫዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 2.96 ሲሆን መደበኛ ልይይት 0.56 ነው፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ የተማሪዎቹ ተነሳሽነት መካከለኛ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ነገር ግን በሰንጠረዥ 4 ላይ የተቀመጠው ገላጭ ስታቲስክስ እንደሚያመለክተው የተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ውጤት ከቋንቋ ትምህርት አማካይ የፈተና ውጤት አንፃር ሲታይ የፈተና ውጤቱ አነስተኛ ነው፡፡ ስለዚህ

ተማሪዎቹ ተነሳሽነት ቢኖራቸውም የፈተና ውጤታቸው ግን በቂ የሚባል አይደለም፡፡ የተማሪዎቹ ተነሳሽነት ከፈተና ውጤታቸው ጋር ያልተጣጣመበት ምክንያት የመማር ማስተማሩ ሂደት ከተማሪዎቹ ተነሳሽነት ጋር የተመጣጠነ ስላልሆነ ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የሚማሩት ትምህርት ከተነሳሽነታቸው ጋር የተመጣጠነ ቢሆን ኖሮ የተማሪዎች ተነሳሽነት ከፍተኛ ሆኖ የትምህርት ውጤታቸው ግን አነስተኛ አይሆንም ነበር፡፡

**ኢሊስ** (1995) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት ኖሯቸው የትምህርት ውጤት ዝቅተኛ ከሆነ ዝቅተኛ ተነሳሽነት ዝቅተኛ ውጤት ን፣ ዝቅተኛ ውጤት ደግሞ መልሶ ዝቅተኛ ተነሳሽነትካሉት ሀሳብ ጋር ሀሳብ ጋር ይጋጫል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጥናት ሂደት የተማሪዎቹ ተነሳሽነት ከፍተኛ ሆኖ የትምህርት ውጤታቸው ግን አነስተኛ ስለሆነ ነው፡፡

### 4.2.2 ሚቄና የአንዘቾ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነታቸው ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል?

ከላይ በሰንጠረዥ 4 ላይ በተቀመጠው መረጃ መሰረት ትንተና እንደሚያመለክተው በውስጣዊ፣ በውጫዊና በጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነቶችና በፈተና ውጤት መካከል ዝምድና አልታየም፡፡ ከተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነቶች ከተማሪዎች የፈተና ውጤት ዝምድና ያሳየው ከውህዳዊ ተነሳሽነት ጋር ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ከውህወዳዊ ተነሳሽነት ውጪ ያሉት ውስጣዊ፣ ውጫዊና ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነቶች ከፈተና ውጤቱ ጋር አለመዛመድ በመማር ማስተማሩ ላይ ችግር መኖሩን መገመት ይቻላል፡፡

### 4.2.3 በሚቄና በአንዘቾ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አማርኛን የመማር ተነሳሽነት ልዩነት አለ?

በሁለቱም ትምህርት ቤቶች መካከል አማርኛ የመማር ተነሳሽነት ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ በተደረገው ትንተና መሰረት  በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መካከል የጎላ ልዩነት አልታየም፡፡

# ምእራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳብ

በዚህ ምዕራፍ ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳቦችን ቀርበዋል፡፡

## 5.1 ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ የጉራጊኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የሆኑ የሚቄና የአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የመማር ተነሳሽነትና የትምህርት ውጤት ተዛምዶን መፈተሽ መሆኑ በቀዳሚ ክፍሎች ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ በዚህ መሰረት በጥናቱ ሂደት መልስ እንዲያገኙ የቀረቡት የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

በሚቄና በአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጉራጊኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በእያንዳንዱ የተነሳሽነት አይነት ያላቸው ተነሳሽነት ምን ያህል ነው?
የሚቄና የአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ (አማርኛ) ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ ምን ይመስላል?
በሚቄና በአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መካከል አማርኛን የመማር ተነሳሽነት ልዩነት አለ?

የሚሉ ጥያቄዎች ለመመለስ የፅሑፍ መጠይቅና ፈተና ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ተመርጠው ተግባራዊ በማድረግ ከሚቄና ከአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015ዓ.ም አስረኛ ክፍል ከሚማሩ ተማሪዎች በዕድል ሰጭ የናሙና ዘዴ ከሁለቱም ትምህርት ቤት 80(ሰማኒያ) የጉራጊኛ ቋንቋ አፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊ ተደርገዋል፡፡ የጽሑፍ መጠይቅና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና  የጥናቱ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመሆናቸው አማርኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ለመለካት 38(ሰላሳ ስምንት) መጠይቆችን የቀረበ ሲሆን እነዚህም መጠይቆች በተለያየ ጊዜያት በመስኩ  የተለያየ ጥናት ሲያደርጉ ከነበሩ **ጋርድነር** (2004) ካዘጋጁት የፅሁፍ መጠይቅ በመምረጥ  ለዚህ ጥናት በሚያመች መልኩ ወደ አማርኛ አሻሻሽሎ በመተርጎም ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተናም ተዘጋጅቶ በጥናቱ አማካሪ ና አስረኛ ክፍል በሚያስተምሩ መምህራን ማስተካከያ ተደርጎባቸው በሙከራ ጥናት ታይተው  በጥያቄው ላይ የተነሱ ችግሮች አስፈላጊውን ማስተካከያ ተደረጎባቸው የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ችሎታቸውን ለመለካ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በፅሑፍ መጠይቅና በትምህርት ፈተና የተሰበሰቡትን መረጃዎች ገላጭ እስታቲክሳዊ ዘዴን በመጠቀም

ተተንትነዋል። በዚህ መሰረት የጥናቱ የመጀመሪያ ጥያቄ በተመለከተ የተማሪዎችን አማርኛ የመማር ተነሳሽነት መጠን በጥናቱ እንደታየው የውስጣዊ ተነሳሽነታቸው አማካይ ውጤት 3.54 መደበኛ ልይይት 0.49፣ በውጫዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 2.96 መደበኛ ልይይት 0.56፣ በውህዳዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.08 መደበኛ ልይይት 0.57 እና የጥቅማ  ጥቅማዊ ተነሳሽነታቸው አማካይ ውጤት 3.11 መደበኛ ልይይት 0.60 ነው።ከዚህ በመነሳት የተማሪዎቹ ተነሳሽነት መካከለኛኛ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል።

የጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ በተመለከተ የሚቂና የአንዘቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን የመማር ተነሳሽነት ከትምህርት ፈተና ውጤታቸው ጋር  የታየው ዝምድና ከአማርኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነቶች ውስጥ ከውህዳዊ ተነሳሽነት ብቻ ተጨባጭ ተዛምዶ ያለው መሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡

ሶስተኛው የጥናቱ ጥያቄ በሚመለከት በሚቂና በአንዘቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት በቲ- ስታቲክስ ሲታይ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች መካከል የጎላ ልዩነት አልታየም።

## 5.2 የመፍትሔ ሀሳብ

የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆን በተማሪዎቹ ውጤት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ስለሚያሳድር መምህራን ተማሪዎቻቸውን ሲያስተምሩ አራቱም የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት አይነቶች ባገናዘበ መልኩ ቢያስተምሩ የተማሪዎቹ ውጤት ሊሻሻል ይችላል። በተጨማሪም ከጥናቱ ትንታኔ ለማየት እንደተቻለው የተነሳሽነት ማነስ በተማሪዎች ትምህርት ውጤት ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል። ስለዚህ መምህራን የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለማሻሻል የሚከተሉትን ነጥቦች በመፍተሔ ሀሳብነት ተቀምጧል።

የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለመጨመር መምህራን በራሳቸውና በተማሪዎቻቸው መካከል ያለው ግንኙነት ትህትና በተላበሰ መልኩ ሲሆን የተማሪዎችን ተነሳሽነት የተሻለ እንደሚሆን በመረዳት መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር በዚህ መልኩ ቢቀራረቡና ትምህርቱም በዚህ መልኩ ቢያቀርቡ ተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በጉጉት እንዲጠብቁ በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎችን ስሜትና ፍላጎት ሊቀሰቅሱ የሚችሉ  አዝናኝ ነገሮች በትምህርቱ ጣልቃ እያስገቡ  ቢያስተምሩ

ተማሪዎች የተሳትፎ መጠን ሲጨምር ተማሪዎች እንዲወያዩና እንዲተጋገዙ ስለሚያነሳሳቸው መምህራን ተማሪዎችን በክፍል ተማሪዎች ተሳትፎ እንዲያደርጉ ቢያግዟቸው

ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት በፆታ ልዩነት እንዳይፈጠር የሁለተኛ ቋንቋ መምህራን የወንድና የሴት ተማሪዎችን ፍላጎት በመለየት ድጋፍ ቢያደርጉላቸው

የሁለተኛ ቋንቋ መምህራን ለተማሪዎች የሚያቀርቡላቸውን ትምህርት ወንድና ሴት ተማሪዎች ፍላጎት እንዲሁም አራቱም የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት አይነቶች መሰረት ያደረገ ቢሆን የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት እንዳይኖር የሚያደርጉ እንቅፋቶችን ለመቀነስ የሁለተኛ ቋንቋ መምህርን እና ሌሎችም ተመራማሪዎች የዚህ ጥናት ውጤት መሰረት በማድረግ የተማሪዎችን ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት እና የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ተዛምዶ ላይ ጥናት ቢያደርጉ

## ዋቢ ጽሑፎች

ተስፋዬ ኦላና፡፡ (2014)፡፡ በኢሊባቦር ዞን በሃሩሙና በሶንጣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነትና የውጤት ተዛምዶ፡፡ ለማስተርስ ድግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡(ያልታተመ)፡፡

አበበ ከበደ፡፡ (2003)፡፡ የመሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለው ዝምድና፡፡ ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

እሸቱ ወንድሙ፡፡ (1997)፡፡ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በውጠየታቸው መካከል ያለ ግንኙነት (በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን)፡፡ ለማስተርስ ድግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ክፍሌ ሰበረው፡፡ (2002) ፡፡ አፋቸውን በጉምዝኛ ቋንቋ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸው ተነሳሽነትና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ተዛምዶ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ፡፡ ባህር ዳርዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያለታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (1996)፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡ ባህርዳር፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዘሪቱ አስፋው፡፡ (2003) ፡፡አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የመማር ተነሳሽነት እና የውጤት ተዛምዶ በጋሞኛ ቋንቋ አፈፊት ተማሪዎች፡፡ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡ ባህዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡(ያልታተመ)፡፡

Brown H.D. (1994) Principles of language learning and teaching (3rd Ed). USA: san farancisco state University.

Brown H.D (1997) Principles of language learning and teaching (2nd Ed) New Jersey, premire Hall

Brown.H.D, (2000), Principles of language learning and teaching(second Ed) USA. longmanlnc.

Elliot, J.G. et al (2005) Motivation, engagement and education performance.international perspective on the contexts for learning newyork; pellagara.

Ellis, R. (1994).The study of second language Acquisiton. Oxford: oxford University Press.

Ellis. R. (1995). Understanding Second Language Acquisition (10th Ed) Hong Kong: Oxford University Press.

Ellis, R (1997). Second Language Acquisition. Oxford: oxford University Press.

Gardner, R.C (1985).Social Psycology and Scond Language Learning: The role of Attitudes and Motivation. London: Arnold.

Gardner, R.C. (2001). Integrative Motivation and Second Language Acquisition. In Z. Dorneyei and R. Schmitd (Eds). Motivation and Second Language Learning. Hondulu: University of awai.

Gardner .R.C (2003). Attitudes, motivation and second language learning. Ameta.Analasis of Studies.

Gardner, R.C (2004). Attitude/Motivation Test Battery: Intrnational AMTB Research Project. The University of Western ontario. Canada. Retrieved April 2011.

Harmer, J. (1991) The practice of English language teaching. London. Longman

Little Wood. W (1981). Communicative Language Teaching Cambrige: cambrige Universty Press.

Noels, K. (2001).New orientations In Language Learning Motivation: Towards amodel of intrinsic, extrinsic and integrative orientation and Motivation. In Z. Dorneyei and R.schemitd (Eds.), Motivations and Second Language Acquisition (Second Language Teaching and Curriculum Center Report). Honola: Teaching and Curriculum Center.

Noels,K.A.(2003) "learning Spanish as asecond language: learners orentations and perception of their teachers comunicatio stayel. In Z Dorny(ed).Attitudes, oreintations and motivations in language learning pp.

Norris-Holt J. (2001) motivation as contributing factor in second langue acquisition. Retreved April 6,2001, Current issue. Activities for ESL students.Things for ESL teachers. Jacqui Japan(at) Hotmail, Japan, the internet TESOL Journal.

Pintrich. R. (2002). Motivation In Education Theory, Research and Application. New York: Mirill Prentice Hall. Scott Kissau.(n.d) gender difrence in second language motivation, an investigation of micro and Macro-level infuences.Refrieved april 5,2011.

Williyam, M.M, Burden, B(1997) Psycology for language teachers. Asocial constractivia approach. Cambrige oxford university press.

# አባሪዎች

**አባሪ አንድ፡ የፅሁፍ መጠይቅ**

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**አማርኛ ቋንቋ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**በጉራጌ ዞን በእኖር ኤነር መገር ወረዳ በሚቄና ነአንዘቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ**

***ውድ ተማሪዎች፦*** *የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነትና የውጤት ተዛምዶ በሚል ርዕስ ለሚካሄደው የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ መረጃ ለማግኘት ነው፡፡*

በውስጡ የተካተቱት ጥያቄዎች ቁጥር ብዛት 38 ሲሆኑ በዚህ መጠይቅ ለቀረቡላችሁ ጥያቄዎች የራሳችሁን ፍላጎት ብቻ በትክክል የሚያንፀባርቁትን ምላሾች ብቻ በመምረጥ ለጥናቱ ዓላማ መሳካት የበኩላችሁን እንድታበረክቱ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡ ውድ ጊዜያችሁን ሰጥታችሁ ይህን መጠይቅ ለመሙላት ፍቃደኛ በመሆናችሁ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

**አጠቃላይ መመሪያ**

1.በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

2. የፅሁፍ መጠይቁን ከሌሎች ጓደኞች ጋር አመሳስሎ መመለስ አይቻልም፡፡

**ክፍል አንድ፡** ዳራዊ መረጃ፡ አንተን(አንቺን) በሚመለከት ትክክል የሆነውን በቀረበው ባዶ ቦታ ውስጥ (√) ምልክትበማድረግ አረጋግጥ(አረጋግጪ)፡፡

ፆታ፡ ወንድ------ ሴት-----

የክፍል ደረጃ-----

የትምህርት ቤት ስም፡ ሚቄ------ አንዘቾ-------

የአፍ መፍቻ ቋንቋ፡ ጉራጊኛ------- አማርኛ-------

**ክፍል ሁለት፡**ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን ዓ.ነገሮች ካነበብክ (ሽ) በኋላ ከቀረቡት አማራጭ መልሶች በቁጥር የተሰየሙና ቁጥሮችም የመስማማት ደረጃዎችን ይወክላሉ፡፡ እናንተ ለጥያቄዎቹ መልስ ይሆናሉ ብላችሁ በምትስማሙበት አማራጭ ትይዩ (√) በማስቀመጥ መልስ ስጡ፡፡

5 በጣም እስማማለሁ 4 እስማማለሁ

3 በመጠኑ እስማማለሁ 2 አልስማማም

1 ፈፅሞ አልስማማም

| ተ.ቁ | መጠይቆች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አማርኛን መማር ደስ ይለኛል፡፡ | | | | | |
| 2 | ወላጆቼ አማርኛን እንድማር ያበረታቱኛል፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | አማርኛ መማር ከአማርኛቋንቋ ተናጋሪ ወገኖች ጋር በ ለመግባባት ይጠቅማል፡፡ | | | | | |
| 4 | አማርኛ ቋንቋ መናገር መቻሌ በማህበረሰቡ ዘንድ ቅቡልነት ሊኖረኝ የሚችለው አማርኛ ቋንቋ መናገር በመቻሌ ነው | | | | | |
| 5 | በሁሉም ዘርፍ አማርኛ ቋንቋ ለማወቅ ምኞት አለኝ | | | | | |
| 6 | ወላጆቼ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያልገባኝ ነገር ካለ ከመምህሬ ጠይቄ መረዳት እንድችል ይገፋፉኛል፡፡ | | | | | |
| 7 | አማርኛ መማሬ ለእኔ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ስነ- ፅሁፎች ና ስነ-ጥበቦች ለመረዳት ስለሚረዳ ነው፡፡ | | | | | |
| 8 | አማረኛ የምማረው በአማርኛ ቋንቋ የተሰሩ ፊልሞችንና የአማርኛ ቋንቋ ሙዚቃዎችን ለመከታተል እና ለመረዳት ነው፡፡ | | | | | |
| 9 | አማርኛ ቋንቋ ማወቅ ያለውን ጠቀሜታ ወላጆቼ ይነግሩኛል፡፡ | | | | | |
| 10 | አማርኛ ቋንቋ የሚገለግለው ከተለያዩ ሰዎች ጋር ለመግባባትና ለመገናኘት ያገለግላል፡፡ | | | | | |
| 11 | አማርኛ መማር ይጠቅማል፡፡ ምክንያቱም የቋንቋውን ተናጋሪዎች የኑሮ ስልት በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል፡፡ | | | | | |
| 12 | አማርኛ ቋንቋ መማር የሚያስፈልገው ጥሩ ስራ ለማግኘት ስለሚጠቅም ነው፡፡ | | | | | |
| 13 | አብዛኛው ጊዜዬ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ባውለው ደስተኛ ነበርኩ፡፡ | | | | | |
| 14 | በአማር የተፃፉ ጋዜጦችነና መጽሔቶችን ማንበብ ደስ ይለኛል፡፡ | | | | | |
| 15 | አማርኛ መማር ይጠቅማል፡፡ ምክንያቱም ሌሎች ሰዎች ስለሚያከብሩኝ ነው፡፡ | | | | | |
| 16 | በአማርኛ መምህሬ ታርመው የተመለሱ የቤት ስራዎቼ ስህተቶችን ለማረም አልጨነቅም፡፡ | | | | | |
| 17 | ምክንያቱም የአማርኛ ችሎታዬን ለቤተሰቦቼ፣ ለጓደኞቼ፣ ለመምህሬና ለሌሎችም ለማሳየት አማርኛ ቋንቋ መከታተል እፈልጋለሁ ነው፡፡ | | | | | |
| 18 | በሌሎች ዘንድ እውቅና ለማግኘት አማርኛ መማር ጠቃሚ ነው፡፡ | | | | | |
| 19 | አማርኛ የመማር ፍላጎት የለኝም፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | ወላጆቼ በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በምሰራቸው ተግባራት ይረካሉ፡፡ | | | | | |
| 21 | ፈተና ለማለፍ አማርኛ መማር እፈልጋለሁ ነው፡፡ | | | | | |
| 22 | ወላጆቼ በተቻለኝ መጠን አማርኛ እንድለማመድ ያበረታቱኛል፡፡ | | | | | |
| 23 | አማርኛን አቀላጥፌ መናገር እመኛለሁ፡፡ | | | | | |
| 24 | በአማርኛ ትምህርት ክፍለ-ጊዜያልገባኝን ነገር ካል መምህሬን በጠየቅ እረዳለሁ፡፡ | | | | | |
| 25 | አማርኛ ለመማር ጠንክሬ እሰራለሁ፡፡ | | | | | |
| 26 | ከሰዎች ጋር ለመገናኘትና ጓደኝነት ለመመስረት አማርኛን የምማርበት አንዱ ምክንያቴ ነው፡፡ | | | | | |
| 27 | አማርኛን መማር ጊዜ መግደል ነው፡፡ | | | | | |
| 28 | ወላጆቼ አማርኛ መማር ጠቃሚ እንደሆነ ይገምታሉ፡፡ | | | | | |
| 29 | የአማርኛ ክፍለ ጊዜያት ከሌሎች ትምህርቶች ክፍለ ጊዜያት የበለጠ ያስደስተኛል፡፡ | | | | | |
| 30 | ወላጆቼ እስከመጨረሻ በአማርኛ ትምህርት እንድቀጥል ይመኛሉ፡፡ | | | | | |
| 31 | አማርኛ ከምወዳቸው ትምህርቶች አንዱ ነው፡፡ | | | | | |
| 32 | አማርኛ መማር እፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም ወደተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች ስዘዋወር ለመግባባትይየጠቅመኛል፡፡ | | | | | |
| 33 | አማርኛን የመማር ፍላጎቱ ስለሌለኝ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ሳጠናቅቅ አማርኛ መማር አቆማለሁ፡፡ | | | | | |
| 34 | በአማርኛ ቋንቋ የሚተላለፉ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን በሌሎች ቋንቋዎች ከሚተላለፉ ፕሮግራሞች የበለጠ እከታተላለሁ፡፡ | | | | | |
| 35 | ወላጆቼ አብዛኛውን ጊዜዬን አማርኛለመማር ማዋል እንዳለብኝ ያምናሉ፡፡ | | | | | |
| 36 | አማርኛ መማር ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ለወደፊት ሙያዬ አስፈላጊ ስለሆነ ነው፡፡ | | | | | |
| 37 | ለሌሎች ትምህርቶች ከማውለው ጊዜ ለአማርኛ ቋንቋ የማውለው ጊዜ ይበልጣል፡፡ | | | | | |
| 38 | አማርኛ የምማርበት ዋና ምክንያት ወላጆቼ አማርኛዬን እንዳሻሽል ስለሚፈልጉ ነው፡፡ | | | | | |

## አባሪ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና

በጉራጌ ዞን በእኖር ኤነር መገር  ወረዳ በሚቂ ና በአንዘቾ አስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ለሚካሄደው ምርምር የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንደ መረጃ ለመገልገል የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና

የተፈቀደ ሰዓት፦ 1፡20

## አጠቃላይ መመሪያ

ውድ ተማሪዎች ይህ ፈተና ከመጀመራችሁ በፊት ከዚህ በታች በተዘጋጀው ቦታ ላይ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በተጠየቀው መሰረት በትክክል አሟልታችሁ ፃፉ፡፡ በመቀጠል ፈተናው አምስት

መመሪያዎችን ይዟል። እያንዳንዱ መመሪያ በትትክክል በማንበብ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን ከጥያቄዎቹ ፊት ለፊት በተዘጋጀው መልስ መስጫ ቦታ (------) ላይ አስቀምጡ።

የተማሪው ሙሉ ስም---------------------------------------------- ፆታ--------- የክፍል ደረጃ ------------- የሚማርበት ትምህርት ቤት-------------------------

**ትዕዛዝ አንድ፦ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 1-10 የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ።(20%)**

----------1. ቋንቋ የመግባቢያነት አገልግሎቱ ለሁሉም ፍጡር ነው።

---------- 2. የግል አስተያየት እውነት ላይ የተመሰረተ እና በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል ነው።

----------3. ሀረግ ማለት ከአረፍተ-ነገር የሰፋ እና ከቃል ያነሰ መዋቅር ነው።

---------- 4. "መለኮት" የሚለው ቃል ነፃ ምዕላድ ነው።

----------5. ምሳሌያዊ አነጋገሮች የስነ-ቃል ዘርፍ ናቸው።

---------- 6. ረጅም ልቦለድ ብዙ ሳይጠማዘዝ ቶሎ ቶሎ ወደ ፊት ይገሰግሳል።

----------7. የአንቀፅ ቅረፆች በሀይለ-ቃል መገኛ ቦታ ይወሰናሉ።

----------8. ፍካሪያዊ ፍች ሲባል ስውር ወይም ምስጢራዊ ፍች ለማለት ነው።

---------- 9. ከፅሁፍ ውስጥ አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት ሚነበብ የንባብ አይነት የገረፍታ ንባብ ይባላል።

----------10. ድርብ ትእምርተ- ጥቅስ ተያያዥነት ያላቸው አረፍተ-ነገሮች ለማያያዝ የሚያገለግል የስርዓተ- ነጥብ አይነት ነው።

**ተዕዛዝ ሁለት፦ከተራ ቁጥር 11-20 የቀረቡት ጥያቄዎች የሚከተለውን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ጪ። (20%)**

## ጠቃሚ ምክር

ከዕለታት አንድ ቀን አንድ አዳኝ በወጥመድ አንዲት ዋኔ ይዞ ወደቤቱ ሲመለስ "ወዴት ነው የምትወስደኝ?"ብላ ዋኔዋ ጠየቀችው።አዳኙ "ምን ትጠይቂኛለሽ?አርጄ ልበላሽ ነዋ!" ብሎ መለሰላት። "እንዴት ያለኸው ሞኝ ነህ! አሁን እኔ በልተህ ልተጠግብ ነው ወይስ ልተወፍር? እሰቲ አስተውለህ ተመልከተኝ!ሰውነቴ በጣም ያነሰ ፍጥረት ነኝ። ከጉሮሮህ እንኳን አልወርድም። ይልቅ እንስማማ እኔ የሚጠቅሙህ ሶስት ምክር ልስጥህ። አንተ ደግሞ ማረኝ። በዚህ

ከተስማማን አንዱን አሁን፣ ሁለተኛው ስትለቀኝ ከዛፍ ላይ ሆኜ ፣ ሶስተኛውን ደግሞ እዚያ ማዶ ካለው ዳገት አፋፍ ላይ ተቀምጬ እነግርሃለሁ።

አዳኙም “የመጀመሪያው ምክርሽ ከጠቀመኝ እለቅሽለሁ።“ ኣላት። እሷም “ባመለጠህ ነገር አትፀፀት፤ እንዲሁም አትቆጭ! የመጀመሪያ ምክሬ ይሄ ነው።“ አለችው። ሰው “የልቡን ሲነግሩት የኮረኮሩትን ያህል ይስቃል“ እንደሚባለው ሰውዬውም ከዚህ ምክር ጋር በልቡ ውስጥ የሚጉላላ አንድ ነገር ተቀሰቀሰበትና “እውነት ተናግረሻል፤ምሬሻለሁ ሂጂ!“ብሎ ለቀቃት። እሷም በረረችና ከዛፍ ላይ አርፋ “አንተ ቂል! አንተ ሞኝ! አንተ ተላላ! በዛሬው ስህተትህ እድሜህን ሙሉ ትፀፀታለህ። እውነት ነው ብትበላኝም ትንሽ ነኝና አልጠቅምህም። ነገር ግን ሆዴ ውስጥ ሀያ ወቄት የሚመዝን ዋጋው በጣም ውድ የሆነ አልማዝ አለ። ብታርደኝ ኖሮ እሱን ታገኝ ነበር። አሁን ግን ከመሄዴ በፊት ሁለተኛውን ምክር ልንገርህ። የማይሆነውን ነገር ይሆናል ብልህ በሞኝነት አትመን። እንግዲህ ደህና ሁን ከነሀብቴ ልሂድ!“ ብላው በረረችና ከአፋፍ ላይ አረፈች።

ሰውዬውም ይህንን ሲሰማ “ወይ እኔ! እንዴት ጉድ ሰራችኝ?“ ብሎ እየተናደደ፣ ከንፈሩን እየነከሰ፣ እያጨበጨበ፣ እየጦፈ፣ ተከተላት። ከአፋፍ አጠገብ ደረሰና ቁና ቁና እየተነፈሰ “ምህረት ባደረኩልሽ እንዲህ የሚያናድድ ነገር ትነግሪኛለሽ? የውለታዬ ዋጋ ይህ ነው?“ እየወቀሳት ድንጋይ ወርውሮ ሊገላት አሰበ። ሆኖም ምንም ለማድረግ እንደማይችል ሲረዳ “የአልማዙ ነገር ይቅር። ይልቅስ ሶስተኛው ምክር ንገሪኝና ወደቤቴ ልሂድ።“ አላት። “ሁለቱ ምክሬ ሳትሰራባቸው ሌላ ብጨምርልህ ምን ያደርግልሃል? በመጀመሪያው ባለፈው ነገር እንዳትፀፀትና እንዳይቆጭህ ነገርኩህ። ቀጥዬም የማይሆነውን ነገር ይሆናል ብለህ በሞኝነት አትመን አልኩህ። ነገር ግን ተግባራዊ አላደረካቸውም። በሆዴ ውስጥ አልማዝ አለ ስልህ ከለቀቅከኝ በኂላ ዳግመኛ ልትይዘኝ ባለመቻልህ ተፀፀትክ። ለምንስ ተቆጫለህ? ደግሞም እኔ( ስጋዬ፣ አጥንቴንና ላባዬ ጭምር ብመዘን ሃያ ወቄት ልሆን አልችልም። እንደምን ሃያ ወቄት የሚመዝን በሆዴ ውስጥ የምሸከም ይመስልሃል? የማይሆነውን ነገር ይሆናል ብለህ በሞኝነት አትመን ብዬ ነግሬህ ነበር እኮ! የያዝከውን ሳተሰራበት ሌላ ጨምሩልኝ አትበል! ሶስተኛው ምክሬ ይህ ነው። ሶስተኛው ልጨምር አይገባም ነበር። ግን ከአንተ ይቅር እንጂ ከኔ ሊጎድል አይገባም። እነግዲህ ደህና ሰንብት!“ ብላው በረረች።

(ከበደ ሚካኤል፣ የእውቀት ብልጭታ፣ ከገጽ 114-116 ተሻሽሎየተወሰደ።)

------11. ከሚከተሉት አንዱ ከዋኔዋ የመጀመሪያ ምክር ጋር ይስማማል።

ሀ. ሳለፈ ክረምት ቤት አይሰራም፡፡

ለ. ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ፡፡

ሐ. ላይሞት ይፈራል፣ ላይድን ይሸሻል፡፡

መ. ሳይቸግር፣ ጤፍ ብድር፡፡

------12. አዳኙ ዋኔዋን ሊለቃት የቻለው በምን ምክንያት ነበር?

ሀ. ከመጀመሪያው የዋኔዋ ምክር በመነሳት ሌላ ጠቃሚ ምክር ላገኝ እችላለሁ ብሎ በመገመቱ

ለ. ዋኔዋን በልቶ ከሚያገኘው ጥቅም የሚያገኘው ምክር የሚሻል መሆኑን በመገመቱ

ሐ. ካለው እውቀትና ልምድ ዋኔዎች ጠቃሚ ምክር የሚሰጡ መሆናቸውን ስለሚያውቅ

መ. ምክሯን ከሰማ በኋላ ዋኔዋን እንደገና በዘዴ መያዝ እንደማያቅተው በመተማመኑ

------13. አዳኙ እየተመከረ ስንት ስህተት ፈፀመ?

ሀ. አንድ ለ. አራት ሐ. ሶስት መ. ሁለት

------14. አዳኙ ብልህ ቢሆን ኖሮ--------፡፡

ሀ. ዋኔዋ ከያዛት በኋላ አይለቃትም ነበር፡፡

ለ. መጀመሪያዉኑ ዋኔዋን አድኖ ለመያዝ አያስብም ነበር፡፡

ሐ. የሰማውን ምክር እያገናዘበ ተግባራዊ ያደርግ ነበር፡፡

መ. የመጀመሪያው ምክር ሲነገረው አይስቅም ነበር፡፡

------15. በዋኔዋ ጥቆማ መሰረት የአዳኙን ማመዛዘን አለመቻል የሚገልፀው የትኛው አባባል ነው?

ሀ. ከዋኔዋ ጠቃሚ ምክር አገኛለሁ ብሎ ማሰብና መገመቱ

ለ. ከዋኔዋ ብዙ ምክር ለመስማት እራሱ ማዘጋጀቱ

ሐ. የዋኔዋን አርቆ አሳቢነት በእርጋታ ተመራምሮ ለመረዳት አለመሞከሩ

መ. በዋኔዋ ሆድ ውስጥ ሃያ ወቄት አልማዝ አለ ብሎ መገመቱና መቆጨቱ

------16. በዋኔዋ አገላለፅ አዳኙ -------ሰው ነው፡፡

ሀ. ልበ ሰፊ ለ. ልበ ሙሉ ሐ. ልበ ገር መ. ልበ ጠናና

------17. ዋኔዋ ለአዳኙ በሂይወት ዘመኑ ሁሉ የሚፀፀተው ነገር መኖሩን የነገረችው የት ሆና ነው?

ሀ. እጁ ውስጥ ለ. ዛፍ ላይ ሐ. አፋፍ ላይ መ. ድንጋይ ላይ

------18. የዋኔዋ ሁለተኛ ምክር የሚገልፀው የትኛው ምሳሌያዊ አነጋገር ነው?

ሀ. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች፡፡

ለ. ሰዶ ከማሳደድ የያዙትን ማጥበቅ፡፡

ሐ. ከቁንጫ፣ መላላጫ፡፡

መ. መራጭ፣ ይወድቃል ከምራጭ፡፡

------19. ከሚከተሉት ሀሳቦች የፅሁፉ አጠቃላይ መልዕክት የሚያንፀባርቀው -------ነው፡፡

ሀ. ምክርን አስተውሎ አዳምጦ ካለተገበሩት ዋጋ የለውም፡፡

ለ. ከታናናሽ የሚቀርብ ምክር መሬት ጠብ አይልም፡፡

ሐ. ጠቃሚ ምክር ለማግኘት ሁል ጊዜ ዝግጁ መሆን ይገባል፡፡

መ. ምክር ማዳመጥ አስተዋይ፣ ትጉህና ብልህ ያደርጋል፡፡

------20. ይህ ፅሁፍ ከየትኛው የድርሰት አይነት ይመደባል?

ሀ. አመዛዛኝ ለ. ስዕላዊ ሐ. ተራኪ መ. ገላጭ

**ትዕዛዝ ሶስት፡-ከተራ ቁጥር 21-40 ድረስ ያሉትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢ የሆነውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጥ /ጪ፡፡ (40%)**

------21. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የቃለ-ጉባኤ መገለጫ ነው፡፡

ሀ. እንደተሰብሳቢዎቹ ፍላጎት የሚሻሻል መሆኑ

ለ. እንደተሰብሳቢዎቹ ፍላጎት የሚፃፍ መሆኑ

ሐ. የስበሰባው ሂደት በትክክልና በእውነት መግለፅ

መ. የስብሰባውን ሂደት እንዳለ መዘገቡ

------22. ከሚከተሉት አንዱ አንድ መስሪያ ቤት የተለያዩ ተግባራትን እንዲፈፀምለት ወደ ሌላ መስሪያ ቤት የሚፅፈው ነው።

ሀ. የስራ ደብዳቤ ለ. የሰላምታ ደብዳቤ

ሐ. የውስጥ ማስታወሻ መ. የግል ማስታወሻ

------23. “ሰው ሆኖ ሳይሳሳት የሚኖር የለም፤ አልተፈጠረም------አይፈጠርም። ለባዶ ቦታው ተስማሚ የሚሆነው ስርዓተ-ነጥብ የትኛው ነው?

ሀ. ቅንፍ ለ. አራት ነጥብ ሐ. ነጠላ ሰረዝ መ. ድርብ ሰረዝ

------24. በስርዓተ- ነጥብ አጠቃቀሙ ትክክል የሆነው ዓረፍተ-ነገር የትኛው ነው?

ሀ. የቀሚሴን፣ ጨርቅ፣ልስላሴ፣ ስፌትና የአበባ አጣጣል፣ በጣም ወደውታል።

ለ. የቀሚሴን፣ ጨርቅ፣ልስላሴ፣ ስፌት፣የአበባ አጣጣል በጣም ወደውታል።

ሐ. የቀሚሴን ጨርቅ፣ ልስላሴ፣ ስፌት፣የአበባ አጣጣል በጣም ወደውታል።

መ. የቀሚሴን ጨርቅ ልስላሴ፣ ስፌት ና የአበባ አጣጣል በጣም ወደውታል።

------25. “አስቴር **በጣም ጥቁር** ልጅ አዝላ መጣች።“በሚለው አረፍተ-ነገር የተሰመረበት ሀረግ

ምን አይነት ሀረግ ነው?

ሀ. ስማዊ ሀረግ ለ. መስተዋድዳዊ ሀረግ ሐ. ቅፅላዊ ሀረግ መ. ግሳዊ ሀረግ

-------26. **“ዳለቻ“** የሚለው ቃል የአማርኛ ቋንቋ ከኦሮምኛ ቋንቋ የወሰደው ነው ብንል፣ ክስተቱ ምንን ይጠቁማል?

ሀ. ቋንቋ ስርዓታዊ መሆኑ ሐ. ቋንቋ ተዋዋሽ መሆኑ

ለ. ቋንቋ ዘፈቀዳዊ መሆኑ መ. ቋንቋ ምሉዕ መሆኑ

------27. ጦጣ በሚለው ስም ላይ -------የሚል ቅጥያ ሲጨመር የውሻው ጾታ ይታወቃል፡፡

ሀ. -ኣችን ለ. -ኤ ሐ-ኦችን መ. -ኢቱ

------28. ከሚከተሉት አንዱ ትእዛዛዊ አረፍተ-ነገር ነው፡፡

ሀ. ድህነት ቀንደኛ ጠላታችን መሆኑ አውቀው ለስራ ተነቃነቁ፡፡

ለ. ጨዋታችሁን አቁሙናና ቤተ-መጻህፍት ገብታችሁ አንብቡ፡፡

ሐ. ካለዘሩ ማጨድ ስለሌለ በርትቶ መስራት ጠቃሚ ነው፡፡

መ. ሰፈርተኛው ሁሉ ወገቡን አስሮ ለልማት ተነሳሳ፡፡

------29. ቀጥሎ ከቀረቡት አረፍተ- ነገሮች መካከል ውስብስብ አረፍተ-ነገር የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ፈተና ስለወደቀች ትምህርቷን አቋረጠች፡፡

ለ. ወተት እርጎ፣ አይብ ና ቅቤ ይወጣዋል፡፡

ሐ. ኢትዮጵያ የልማት መርሀ-ግብሮችን ነድፋለች፡፡

መ. ስልጣኔ የሚለው ቃል ሰዎች በቀላሉ አይረዱትም፡፡

------30. "ተናገር አንተ ሀውልት አክሱም ላይ ያለኸው፣ እስከ ዛሬ ድረስ ብዙ ጉድ ያየኸው፡፡" የሚለዉ ዘይቤ ምን አይነት ዘይቤ ነው?

ሀ. አነፃፃሪ ዘይቤ ለ. ግነት ዘይቤ ሐ. እነቶኔ ዘይቤ መ. ሰውኛ ዘይቤ

------31. "ቤቱ ፈረስ ያስጋልባል፡፡" የሚለው------ ዘይቤ ነው፡፡

ሀ. ሰውኛ ለ. እንቶኔ ሐ. ግነት መ. አያዎ

------32. ከሚከተሉት ውስጥ የግጥም ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ቁጥብ አይደለም ለ. ምጣኔ አለው ሐ. ዜማ አለው መ. ምት አለው

--------33. የሰንጎ መገን ግጥም በሐረግ ስንት ቀለም አለው?

ሀ. 6 ለ. 5 ሐ. 4 መ. 2

------34. ግጥም ተለክቶ የሚያልቀው በ------ውስጥ ነው፡፡

ሀ. ቀለም ለ. ስንኝ ሐ. ሐረግ መ. ቤት

------35. **"አንገታም"** የሚለው ቃል ሁለት ፍች ሊሰጥ የሚችለው ምን ሲሆን ነው?

ሀ. "ን"ጠብቆ ሲነበብ ና "ገ"ላልቶ ሲነበብ ለ. "ታ"ጠብቆ ና ላልቶ ሲነበብ

ሐ. "ገ" ጠብቆና ላልቶ ሲነበብ መ. "ን" ጠብቆ ና ላልቶ ሲነበብ

-----36. "ቀደም ሲል ለሁለተኛ ደረጃ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለማስተማሪያነት ከተዘጋጁት መጸሀፍትይልቅ በአሁኑ ሰዓት የሚዘጋጁት ከተለያዩ ሁኔታዎች አንፃር የተሻሉ ናቸው፡፡" የሚለውን መነሻ ሀሳብ ይዞ ለመፃፍ ከሚከተሉት የትኛው የድርሰት አይነት ተግባራዊ ይደረጋል?

ሀ. ስዕላዊ ድርሰት ለ. አመዛዛኝ ድርሰት ሐ. ገላጭ ድርሰት መ. ተራኪ ድርሰት

------37. የአንድ አንቀፅ ቅርፅ የሚወሰነው በምንድ ነው?

ሀ. በያዘው ፍሬ ነገር ሐ. በመዘርዝሮቹ አገላለፅ

ለ. በሀይለ-ቃሉ መገኛ ቦታ መ. በፅሁፉ ርዕስ

------38. "አየለ ጮቅ ነው፤ ሳይታወቅበት ባላጋራዎቹንእንዴት ማሸነፍ እንደሚችል አሳምሮ ያውቃል፡፡" በሚለው አረፍተ- ነገር ውስጥ ፍካሬያዊ ፍች ያለው ቃል ---- ነው፡፡

ሀ. አሳምሮ ለ. ባላጋራዎቹን ሐ. ጮቅ መ. ማሸነፍ

-------39. በቃላት አደራደር ስርዓቱ ትክክለኛ መልዕክት የሚያስተላልፈው የትኛው ዓረፈተ- ነገር ነው?

ሀ. ሴቶቹ የተቀቡት ሽቶ መዓዛው ያውዳል፡፡ ለ. ሴቶቹ የተቀቡት ሽቶ የመዓዛው ያውዳል፡፡

ሐ. ሴቶቹ የተቀቡተ መዓዛ የሽቶ ያውዳል፡፡ መ. ሴቶቹ የተቀቡት የሽቶ መዓዛ ያውዳል፡፡

------40. ከሚከተሉት አባባሎች መካከል አንዱ ቀስቃሽ ነው፡፡

ሀ. ኤች አይቪ በደማቸው የሚገኝ እናቶች ተገቢውን ህክምናና ምክር ከተከታተሉ ከቫይረሱ ነፃ የሆነ ልጅ   ይወልዳሉ፡፡

ለ. በ2015 ዓ.ም ከዘጠኝ ሺ ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያዊያን የኤች አይቪ የምክርና የምርመራ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

ሐ. አንድም ሰው በኤች አይቪ እንዳይያዝ ና እንዳይሞት ሁሉም ሀላፊነቱ ይወጣ፡፡

መ. ኤች አይቪ በዓለም ላይ መኖሩ ከተረጋገጠ አርባ ሁለት አመታት አስቆጠረ፡፡

**ትዕዛዝ አራት፡የሚከተሉትን ጅምር ስንኞች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡(10%)**

41. ላም ባለዋለበት ---------------------------------------------------------------------

42. ሆድ ለባሰው-------------------------------------------------------------------------

43. አፍጫ ሲመታ----------------------------------------------------------------------

44. ባለቤቱ ካልናቁ--------------------------------------------------------------------

45. አካሄዱን አይተው-------------------------------------------------------------------

**ትዕዛዝ አምስት፡የሚከተሉትን አረፍተ-ነገሮች ውስብስብ ወይም ተራ አረፍተ-ነገር በማለት ለይ/ለዩ፡፡(10%)**

46. በጓደኛዋ ሰርግ ለመታደም በባቡር ወደ ከተማ ሄደች፡፡-----------------------------------

47. ሰዎቹ እየተሯሯጡ ሲመጡ ልጆቹ ደነገጡ፡፡---------------------------------------------

48. ሙሐመድ ታታሪ ሰው ነው፡፡----------------------------------------------------------

49. ፀጋ አሮጌውን መኪና አሳድሶ ለታላቅ ወንድሙ ሰጠው፡፡---------------------------------

50. በረሀብ የተጎዱትን ወገኖቹን ለመታደግ እርዳታ ጠየቀ፡፡----------------------------------

# አባሪ ሶስት ተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | 31 | 32 | 33 | 34 | 35 | 36 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| M | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 2 | 5 | 3 | 2 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 1 | 3 | 5 | 5 | 4 | 2 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 |
| M | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 3 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 3 | 5 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 5 | 4 | 4 | 3 | 5 | 5 | 1 | 3 | 4 | 3 |
| M | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 2 | 3 | 5 | 5 | 2 | 4 | 4 | 5 | 3 | 4 | 3 | 5 | 3 | 5 | 3 | 4 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 1 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 |
| M | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 4 | 4 | 5 | 3 | 5 | 3 | 5 | 1 | 3 | 5 | 1 | 1 | 3 | 5 | 2 | 5 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 |
| M | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 3 | 3 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 3 | 5 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 5 | 3 | 3 | 3 |
| M | 19 | Gura | Amha | M2ndschoo | 2 | 1 | 5 | 5 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 | 5 | 4 | 4 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 |
| M | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 4 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 |
| M | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 5 | 1 | 4 | 2 | 4 | 5 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 3 | 5 | 5 | 2 | 4 | 5 | 4 |
| M | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 3 | 2 | 1 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 5 | 2 | 3 | 1 | 5 | 3 | 5 | 4 | 4 | 2 | 3 | 2 | 4 | 4 | 2 | 2 | 4 | 3 |
| M | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 4 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 5 | 2 | 2 | 1 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 4 |
| M | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 4 | 5 | 5 | 3 | 5 | 4 | 3 | 2 | 2 | 5 | 1 | 5 | 3 | 3 | 1 | 3 | 5 | 1 | 4 | 3 | 1 | 3 | 5 | 1 | 4 | 3 | 5 | 3 | 5 | 3 | 5 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 |
| M | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 4 | 2 | 5 | 5 | 2 | 5 | 2 | 5 | 5 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 3 | 5 | 4 | 5 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 5 | 4 | 3 | 5 | 5 | 2 |
| M | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 4 | 3 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 5 | 3 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 |
| M | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 4 | 5 | 5 | 3 | 2 | 5 | 5 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 | 4 | 5 | 1 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 5 | 3 | 4 | 3 | 3 | 5 | 2 | 2 |
| M | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 4 | 3 | 3 | 4 | 5 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 3 | 5 | 3 | 4 | 5 | 3 | 2 | 3 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 5 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 5 |
| M | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 5 | 3 | 4 | 5 | 1 | 2 | 4 | 3 | 5 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 2 | 5 | 3 | 3 | 4 | 2 | 5 | 2 | 5 | 3 | 4 |
| M | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 5 | 4 | 2 | 3 | 5 | 1 | 3 | 2 | 5 | 1 | 4 | 2 | 3 | 2 | 1 | 5 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 1 | 3 | 5 | 2 | 4 | 1 | 3 | 3 | 4 | 1 |
| M | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 2 | 4 | 5 | 3 | 3 | 4 | 1 | 1 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 2 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 1 | 3 | 1 | 3 | 5 | 3 | 5 | 5 | 2 | 5 | 2 | 3 |
| M | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 3 | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 2 | 2 | 4 | 4 | 2 | 4 | 5 | 1 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 5 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 5 | 4 | 1 | 5 | 2 | 2 |
| M | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 2 | 4 | 3 | 1 | 5 | 4 | 2 | 3 | 5 | 1 | 4 | 3 | 2 | 5 | 1 | 4 | 2 | 5 | 1 | 4 | 2 | 3 | 4 | 1 | 5 | 4 | 2 | 3 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 5 | 4 | 1 |
| F | 17 | Gura | Amha | MM2ndschool | 4 | 5 | 5 | 3 | 4 | 5 | 5 | 2 | 3 | 5 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 1 | 3 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 4 | 4 | 2 | 5 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 |
| F | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 3 | 2 | 2 | 5 | 3 | 4 | 2 | 3 | 1 | 2 | 1 | 4 | 5 | 1 | 3 | 2 | 1 | 5 | 3 | 2 | 3 | 4 | 5 | 4 | 2 | 5 | 2 | 5 | 2 | 3 | 1 | 5 | 3 | 2 | 3 |
| F | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 3 | 5 | 2 | 2 | 4 | 2 | 4 | 5 | 2 | 3 | 2 | 1 | 4 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 1 | 4 | 2 | 1 | 5 | 1 | 2 |
| F | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 4 | 4 | 2 | 3 | 5 | 3 | 2 | 3 | 5 | 2 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 5 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 1 | 3 | 3 | 2 |
| F | 17 | Gura | Amha | m2ndschool | 5 | 2 | 5 | 2 | 5 | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 5 | 2 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 2 | 4 | 4 | 3 | 4 | 5 | 3 | 1 | 5 | 3 | 3 |
| F | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 1 | 3 | 4 | 5 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 2 |
| F | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 3 | 5 | 4 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 | 5 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 5 | 4 | 1 | 2 | 3 | 3 |
| F | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 5 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 5 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 5 | 2 | 4 |
| F | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 4 | 3 | 5 | 2 | 5 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 5 | 3 | 3 | 4 | 5 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 1 | 4 | 3 | 2 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| F | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 1 | 3 | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 | 5 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 |
| F | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 3 | 4 | 4 | 2 | 5 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 5 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 5 |
| F | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 1 | 3 | 3 | 4 | 1 | 3 | 3 | 1 | 2 | 1 | 1 | 5 | 3 | 2 | 3 | 5 | 3 | 5 | 1 | 5 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 |
| F | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 2 | 3 | 5 | 5 | 2 | 4 | 5 | 1 | 3 | 1 | 1 | 4 | 2 | 1 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 2 | 5 | 2 | 4 |
| F | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 3 | 4 | 4 | 3 | 5 | 5 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 1 | 5 | 3 | 1 | 3 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 5 | 1 | 4 | 3 | 5 |
| F | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 3 | 1 | 1 | 4 | 3 | 5 | 1 | 3 | 5 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 5 | 3 | 3 |
| F | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 |
| F | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 1 | 3 | 4 | 5 | 2 | 4 | 4 | 2 | 5 | 2 | 1 | 5 | 3 | 2 | 3 | 5 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 4 | 1 | 5 | 3 | 2 |
| F | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 5 | 3 | 4 |
| F | 18 | Gura | Amha | M2ndschool | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 | 1 | 4 | 5 | 3 | 3 | 5 | 5 | 2 | 1 | 5 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 3 | 5 | 3 | 4 | 2 | 5 | 1 | 5 | 4 | 2 | 5 | 3 | 4 |
| F | 17 | Gura | Amha | M2ndschool | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 5 | 5 | 2 | 3 | 5 | 3 | 3 | 3 | 5 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 5 | 3 | 4 | 5 | 5 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 5 |
| M | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 4 | 3 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 5 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 |
| M | 19 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 3 | 5 | 5 | 3 | 5 | 3 | 1 | 2 | 5 | 2 | 1 | 2 | 4 | 1 | 1 | 3 | 1 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 1 | 3 | 3 | 5 | 2 | 3 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 |
| M | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 4 | 5 | 2 | 5 | 4 | 4 | 2 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 2 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 5 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 2 | 4 | 2 | 3 |
| M | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 3 | 3 | 2 | 2 | 5 | 5 | 4 | 2 | 4 | 5 | 3 | 2 | 4 | 5 | 2 | 5 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 5 | 5 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 2 | 5 | 5 | 4 |
| M | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 2 | 5 | 2 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 2 | 4 | 3 | 3 | 5 | 3 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 5 | 3 | 3 | 4 |
| M | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 4 | 3 | 5 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 5 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 3 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 5 | 3 | 4 | 5 | 4 |
| M | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 2 | 3 | 5 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| M | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 4 | 2 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 3 | 2 | 5 | 5 | 4 | 3 | 3 | 1 | 2 | 4 | 5 | 4 | 2 | 3 | 2 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 2 | 3 | 2 | 4 | 4 | 5 | 4 | 2 | 5 |
| M | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 3 | 3 | 5 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 5 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 5 | 3 | 2 |
| M | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 3 | 2 | 5 | 5 | 2 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 3 | 5 | 2 | 3 | 5 | 4 | 5 | 5 | 3 | 2 | 5 | 2 | 3 | 4 | 3 | 5 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 5 |
| M | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 1 | 1 | 2 | 5 | 1 | 3 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 5 | 5 | 1 | 5 | 3 | 4 | 5 | 1 | 2 | 1 | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 3 | 4 | 2 | 4 | 1 | 1 | 2 | 3 | 2 |
| M | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 3 | 2 | 5 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 2 | 5 | 4 | 2 | 3 | 3 | 2 | 5 | 4 | 3 | 4 | 2 | 1 | 2 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 4 | 5 | 2 | 5 | 2 | 4 |
| M | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 2 | 2 | 4 | 3 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 3 | 3 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 5 | 1 | 1 | 5 | 3 | 5 |
| M | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 1 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 5 | 1 | 2 | 2 | 2 | 5 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 5 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 1 | 1 | 1 | 4 | 2 |
| M | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 2 | 5 | 3 | 3 | 3 | 4 | 1 | 1 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 2 | 5 | 2 | 3 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 2 | 4 | 4 | 2 | 5 | 2 | 3 |
| M | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | 5 | 3 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 5 | 1 | 4 | 4 | 5 |
| M | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 2 | 4 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 | 5 | 2 | 4 | 3 | 4 |
| M | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 3 | 2 | 5 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 5 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 5 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 1 | 5 | 2 | 4 |
| M | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 3 | 4 | 5 | 3 | 4 | 3 | 1 | 5 | 5 | 4 | 3 | 1 | 4 | 1 | 1 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 | 2 | 5 | 4 | 2 | 4 | 4 | 5 |
| M | 19 | Gura | Amha | A2ndschool | 2 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 2 |
| F | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 2 | 5 | 3 | 1 | 3 | 5 | 5 | 5 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 5 | 4 | 2 | 3 | 2 | 1 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| F | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 2 | 2 | 2 | 2 | 5 | 4 | 2 | 4 | 4 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 1 | 4 | 3 | 4 |
| F | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 4 |
| F | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 5 | 3 | 3 | 5 | 1 | 2 | 4 | 3 | 5 | 5 | 4 | 3 | 3 | 5 | 5 | 5 | 3 | 5 | 3 | 5 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 5 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 1 | 4 | 2 | 5 |
| F | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 5 | 1 | 4 | 5 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 1 | 2 | 5 | 3 | 1 | 4 | 5 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 5 | 5 | 1 | 3 | 2 | 4 |
| F | 17 | Gra | Amha | A2ndschool | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 5 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 3 | 4 | 3 | 5 | 4 | 2 | 4 | 2 | 2 |
| F | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 2 | 3 | 5 | 5 | 3 | 4 | 5 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 1 | 3 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 1 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 5 | 3 | 5 |
| F | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 3 | 2 | 5 | 4 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 1 | 1 | 5 | 2 | 1 | 3 | 5 | 5 | 5 | 2 | 5 | 3 | 1 | 1 | 5 | 2 | 1 | 4 | 1 | 1 |
| F | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 2 | 4 | 2 | 3 | 2 | 5 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 2 | 3 | 2 | 2 | 4 | 2 | 1 | 2 | 5 | 3 | 3 | 5 | 3 | 4 | 2 | 3 | 5 | 3 | 2 | 5 | 2 | 3 |
| F | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 5 | 2 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 1 | 1 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 5 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 1 | 5 | 2 | 3 |
| F | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 2 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 4 | 2 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 |
| F | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 | 2 | 4 | 4 | 5 | 2 | 3 | 4 | 1 | 5 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 5 | 3 | 5 | 3 | 5 | 2 | 4 | 1 | 1 | 4 | 2 | 3 |
| F | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 3 | 5 | 5 | 3 | 1 | 4 | 2 | 5 | 2 | 4 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 5 | 5 | 1 | 5 | 3 | 4 |
| F | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 1 | 1 | 3 | 3 | 5 | 3 | 1 | 3 | 5 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 2 | 4 | 4 | 1 | 4 | 2 | 4 |
| F | 18 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 2 | 5 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 5 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 1 | 4 | 3 | 3 |
| F | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 5 | 5 | 3 | 3 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 3 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 3 | 4 | 2 | 5 | 3 | 3 | 5 | 2 | 3 |
| F | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 5 | 3 | 5 | 5 | 5 | 3 | 4 | 5 | 5 | 3 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 3 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 |
| F | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 2 | 1 | 5 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 2 | 3 | 2 | 4 | 5 | 2 | 5 | 2 | 5 |
| F | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 5 | 4 | 5 | 3 | 3 | 4 | 5 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 5 | 2 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 3 | 2 | 5 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 |
| F | 17 | Gura | Amha | A2ndschool | 4 | 2 | 5 | 4 | 3 | 3 | 5 | 1 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 4 | 1 | 2 | 2 | 1 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 5 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 4 | 2 | 4 | 2 | 2 |

## አባሪ አራት የመጠይቁ አስተማማኝነት

| | |
|---|---|
| የአስተማማኝነት መጠን | የመጠይቆቹ ብዛት |
| 0.825 | 38 |

## አባሪ አምስት የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የፈተና ውጤት

| ተ.ቁ | ፆታ | ት/ቤት | 100% ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 30 |
| 2 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጀ | 50 |
| 3 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 76 |
| 4 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 50 |
| 5 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 34 |
| 6 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 74 |
| 7 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 48 |
| 8 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 40 |
| 9 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 60 |
| 10 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 62 |
| 11 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 60 |
| 12 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 42 |
| 13 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 43 |
| 14 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 52 |
| 15 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 50 |
| 16 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 54 |
| 17 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 52 |
| 18 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 76 |
| 19 | ወንድ | ሚቄ 2ኛ ደረጃ | 30 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 20 | ወንድ | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 34 |
| 21 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 50 |
| 22 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 28 |
| 23 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 50 |
| 24 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 34 |
| 25 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 20 |
| 26 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 28 |
| 27 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 32 |
| 28 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 38 |
| 28 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 42 |
| 30 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 40 |
| 31 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 78 |
| 32 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 49 |
| 33 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 46 |
| 34 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 38 |
| 35 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 42 |
| 36 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 46 |
| 37 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 42 |
| 38 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 45 |
| 39 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 36 |
| 40 | ሴት | ሚቂ 2ኛ ደረጃ | 74 |
| 41 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 62 |
| 42 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 40 |
| 43 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 70 |
| 44 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 49 |
| 45 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 64 |
| 46 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 76 |
| 47 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 66 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 48 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 70 |
| 49 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 50 |
| 50 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 76 |
| 51 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 30 |
| 52 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 50 |
| 53 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 28 |
| 54 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 30 |
| 55 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 56 |
| 56 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 64 |
| 57 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 62 |
| 58 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 66 |
| 59 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 50 |
| 60 | ወንድ | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 62 |
| 61 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 56 |
| 62 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 50 |
| 63 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 76 |
| 64 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 50 |
| 65 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 52 |
| 66 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 46 |
| 67 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 49 |
| 68 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 74 |
| 69 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 42 |
| 70 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 46 |
| 71 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 40 |
| 72 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 26 |
| 73 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 48 |
| 74 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 48 |
| 75 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 47 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 76 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 45 |
| 77 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 62 |
| 78 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 66 |
| 79 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 44 |
| 80 | ሴት | አንዘቸ2ኛ ደረጃ | 45 |

**አባሪ ስድስት፡ ሙዳዬ ቃላት**

| | |
|---|---|
| ተነሳሽነት | Motivation |
| ተዛምዶ | Correletion |
| የትምህርት ውጤት | Education Result |
| ውስጣዊ ተነሳሽነት | Intrinsic |
| ውጫዊ ተነሳሽነት | Extrinsic |
| ውህዳዊ ተነሳሽነት | Integrative |
| ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት | Instrumental |
| የፒርሰን ተዛምዶ | Pearson Correlation |

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ፊርማዬ ያስቀምኩ የድህረ ምረቃ ተማሪ ይህ ጥናት የራሴ መሆኑን እና በጥናቱም የተጠቀሙኩባቸው ምንጮች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ________________________________________

ፊርማ ______________________________________

ቀን ________________________________________